''ቀድሱ ጾመ ወስብኩ ምሕላ ጾምን ቀድሱ
ምህላንም ዐውጁ''
*(ት/ኢዩ ፩፥፲)*

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፩ አጫጭር ዜናዎች

፫ ርእሰ አንቀጽ

፭ ሪፖርታዥ

፯ ቤተ አብርሃም

፲፩ ቃለ መጠይቅ

፲፪ የሕፃናት ዓምድ

፲፭ ትዝብት

፳ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ


## ስምዐ ጽድቅ


የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ በጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442
✉ 80078
<u>አዲስ አበባ</u>

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org



ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ
ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ
ሪፖርተር
ረቂቅ መቻል
የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነር
ግደይ ገብሬ
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ

# ብፁዕ አቡነ ገብርኤል (ዶ/ር) ዐረፉ

*በካሣሁን ለምለሙ*

ብፁዕ አቡነ ገብርኤል (ዶ/ር) ታኅሣሥ ፲፱ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ከአባታቸው ከመምህር ቀሲስ ገብረ ሕይወት ወልደ ሐዋርያት እና ከእናታቸው ወይዘሮ ብርነሽ ቸኮል በቀድሞ የወሎ ክፍለ ሀገር ዋግ ሕምራ አውራጃ ተወለዱ።

ብፁዕነታቸው በተለያዩ የሀገራችን ክፍል ተዘዋውረው የቤተክርስቲያንን ትምህርት ጠንቅቀው ተምረዋል። ወደ ተለያዩ ውጭ ሀገራት በመሄድም የተለያዩ ትምህርቶችን ተምረው ያተጠናቀቁ ሲሆን በሩሲያ ሞስኮብ የቀድሞው ፒተርስበርግ በኋላ ሌኒንግራድ ዩኒቨርስቲ በሃይማኖተ አበው የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። የማስተርስ ዲግሪያቸውንም እንዲሁ በነገረ ክርስቶስ ትምህርት ያገኙ ሲሆን ዶክተሬት ዲግሪያቸውን ደግሞ በነገረ ሥጋዌ አግኝተዋል።

ቀጥሎም ወደ ሰሜን አሜሪካ በመሔድ በፕሪስተን ዩኒቨርስቲ በማስተር ኦፍ ቲዎሎጂ ዲግሪ ተቀብለዋል። ብፁዕነታቸው በምንኵስና የቅድስና ሕይወት ጉዞ የጀመሩትና ለታላቁ ማዕረግ እንዲደርሱ የእግዚአብሔር ጥሪ የደረሳቸው በ፲፱፻፷፩ ዓ.ም ሲሆን በዚህ ዓመት ወደ ደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለሃይማኖት አንድነት ገዳም በመሔድ መንኵሰዋል። በመቀጠልም መስከረም ፮ ቀን ፲፱፻፷፪ ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ዘመነ ፕትርክና ከብፁዕ አቡነ ያዕቆብ የወለጋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ቅስና እና ቁምስናን ተቀብለዋል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራዶኦ ኮሚሽን ዋና ጸሐፊ ቀጥሎም የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የካህናት አስተዳደር መምሪያና መንፈሳዊ አገልግሎት መምሪያ ኃላፊ ሆነው በማገልገል ላይ ሳሉ ጥር ፬ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ/ም በቅዱስ

ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ውሳኔ ዶር አባ ኢያሱ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አባ ገብርኤል ተብለው የመንፈሳዊ ኮሌጅ ኤጲስ ቆጶስ (ዲን)፤ የድሬዳዋ እና አካባቢው ኤጲስ ቆጶስ ተብለው ተሾሙ። በድሬዳዋ ሀገረ ሰብከትም ለአንድ ዓመት ያህል ከአገለገሉ በኋላ በ ፲፱፻፹፫ ዓ/ም የኤርትራ ክፍለ ሀገር ሀገረ ሰብከት ሊቀ ጳጳስ በመሆን ለተከታታይ ሦስት ዓመታት አገልግለዋል።

ብፁዕነታቸው በአጠቃላይ ቤተክርስቲያንን በተለያዩ የአገልገሎት ዘርፍ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር በትጋት ያገለግሉ ሲሆን። ከ፳፻፫ ዓ.ም ጀምሮ ወደ ሲዳማ፣ ጌድኦ፣ አማሮና ቡርጂ ዞን ሀገረ ስብከት ተልከው እስከ ጥቅምት ፳፻፲፫ ዓ.ም ከላይ በተጠቀሱት። አህጉረ ሰብክት ተዛውረው በርካታ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶችን በማከናወን ቤተ ክርስቲያንን እያገለገሉ ይገኙ ነበር።



ብፁዕ አቡነ ገብርኤል (ዶ/ር)

ብፁዕነታቸው በጸበልና በሕክምና ሲረዱ ቆይተው ኅዳር ፳፮ ቀን ፳፻፲፫ ዓ/ም ከቀኑ ፰ ሰዓት በተወለዱ በ፹ ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ሥርዓተ ቀብራቸውም ቅዱስ ፓትርያሪኩ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳትና የቤተ ክርስቲያን የበላይ ኃላፊዎች እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸውና ወዳጅ ዘመዶቻቸው በተገኙበት ኅዳር ፳፯ ቀን ፳፻፲፫ ዓ/ም ከጠዋቱ በ፬ በአዲስ አበባ መንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተፈጽሟል።

# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ካራኪን ዳግማዊ ከአራስፅካህ የተፈናቀሉ ክርስቲያኖችን ጎበኙ

*በካሣሁን ለምለሙ*

የአርመንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ካራኪን ዳግማዊ በአርመንያና በአዘርባጃን መካከል በተካሄደው ጦርነት ምክንያት የተፈናቀሉ ምእመናንን መጎብኘታቸው ኦርቶዶክስ ኮግኔት ፔጅ አስነብቧል።

ከወራቶች በፊት በነበረው ጦርነት ምክንያት በርካታ አርመንያውያን ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች አካባቢያቸውን ለቀው በአርመንያ ባሉ አህጉረ ስብከት በሚገኙ አጥቢያዎች ተጠልለው ይገኛሉ። ቅዱስ ፓትርያርኩም ክርስቲያኖች ተጠልለው ከሚገኙበት ቦታ በአንዱ ተገኝተው ያጽናኑ ሲሆን ተገቢው ጥበቃና ክብክብካቤ እየተደረገላቸው መሆኑንን ማረጋገጥ እንደቻሉ ዘገባው አመልክቷል።

የአርመንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለተፈናቃዮች የምግብ፣ የልብስና ሌሎች አስፈላጊ ድጋፎችን እያደረገች ሲሆን ተጨማሪ ርዳታ ማድረግ የሚፈልግ ማንኛውም አካል ካለ ደግሞ ‹‹የእችሚአዳጊን ጓደኞች›› በሚለው አድራሻ በኩል ድጋፍ ማድረግ እንደሚቻል ከዘገባው ለመረዳት ተችሏል።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ካራኪን ዳግማዊ

# በፈረሰው በኩል የቆሙ የቤተ ክርስቲያን የቁርጥ ቀን ልጆች

ያሳለፍናቸው ሦስት ዓመታት በተለይ በ፳፻፲፪ ዓ.ም በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የደረሰው ጉዳት ቀላል አይደለም:: ለዘመናት የመንግሥት ለውጥ በተደረገ ቁጥር የጥቃት ዒላማ ሆና የኖረችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አሁንም በተመሳሳይ ሰቆቃን አሳልፋለች:: ካለፉት ተደጋጋሚ ድርጊቶች በመነሣት ጠላቶቿ የመንግሥትን ለውጥ አለዚያም ትንሽ ግርግርን ተገን አድርገው ሊያጠቋት ሠይፍ ይዘው እንደሚነሡ ታዝበናል:: ዛሬም እያስተናገደች ያለችው ይህንኑ ነው:: የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ምእመናንና ምእመናት፣ ሕጻናትና ወጣቶ፣ አዛውንቱና አረጋውያኑ፣ ካህናትም ሳይቀሩ ብዙዎቹ የወቅቱ የጥቃት ሰለባ ሆነው አልፈዋል:: የሰውን ልብ የሚሰብር ግፍ የተፈጸመባቸው፣ ከቤት ከንብረታቸው የተፈናቀሉ፣ ቤታቸው የተቃጠለባቸው ብዙዎች ናቸው:: አብያተ ክርስቲያናቱ ተቃጥለው፣ ካህናቱ ተሰደው ተንገላተው ባቆሚት ሀገር ባይተዋር ሆነው አሳልፈዋል::

በዚያው መጠን በደረሰው ጉዳት እና ጥፋት ልክ ቤተ ክርስቲያን እና ልጆችዋን ለመታደግ የሚችሉትን ሁሉ በማድረግ የማይናቅ አስተዋጽኦ ያደረጉ የቤተ ክርስቲያናችን ልጆች ቁጥር ቀላል አይደለም:: በየቦታው የደረሰውን መጠነ ሰፊ ጥፋት በመከታተልና በማጋለጥ፤ ሊደርስ የሚችለውን የጥፋት ዕቅድም አስቀድሞ መረጃ በመስጠት ብዙ ሥራ ሠርተዋል:: ለተጎዱት በመድረስ ጉዳታቸውን፣ኀዘናቸውን በመካፈል አለኝታ ሆነዋቸዋል:: በተገኘው የመገናኛ ዘዴ ሁሉ የቤተ ክርስቲያንን መከራ ጮኸው ለዓለም አሳውቀዋል:: በጊዜው ድምጽ ላልነበራቸው የቤተ ክርስቲያን ልጆች ድምጽ ሆነዋል:: ቤተ ክርስቲያንን ለመታደግ በግልም በቡድንም የተደረገው ርብርብ የነገን ተስፋ የሚያጭር ለቤተ ክርስቲያን ኩራት፤ ለምእመናንም አርአያ የሆነ፣ ይበል የሚያስብል ሥራ ነውና ሊመሰገኑ ይገባል::

ስለ ክርስትናቸው ከቤተ ክርስቲያን ጥፋት በፊት ራሳቸውን አስቀድመው ሰማዕትነትን ስለተቀበሉት ምእመናን ‹‹ክርስትና ማለት ይህ ነው›› ብለው ለቀረነው ክርስቲያኖች ጽናት እንዲሆነን መስክረውልናል:: በሕይወት ለቀሩት ነገር ግን በጥቃቱ በአንድ ጀንበር ንብረታቸው ለወደመባቸው ፣ ከነበሩበት ከፍተኛ የኑሮ ማማ ላይ ወርደው የሰው እጅ ተመልካች ለሆኑት ምእመናን ቀድሞ በመድረስ፤ የምግብ፣ የልብስ እና የገንዘብ ዕርዳታን በማድረግ የፈረሰ ቤታቸውን የሠሩ የቤተ ክርስቲያን የቁርጥ ቀን ልጆች ዋጋቸው በምን ይተመናል? የተቃጠለውን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ከበፊቱ በተሻለ በመሥራት በፈረሰው በኩል የቆሙ የቤተ ክርስቲያን ልጆች በእምነት እንዴት መቆም እንዳለብን አሳይተውናልና ሊመሰገኑ ይገባል::

የእምነት አርበኛ በሆኑት የቤተ ክርስቲያን ልጆች፤ በኅብረት እና በግል የተደረጉ እርዳታዎች፣ ለመልካም ነገር የተዘረጉ እጆች ባጠቃላይ ሰጪዎችን ብቻ ሳይሆን የተሰጣቸውን ተጎጂዎች በእምነታቸው እንዲጠነክሩ ነገን ተስፋ እንዲያደርጉ ያስቻለ በተግባር የተገለጠ ክርስትናን አሳይተውናል:: ስለ ቅድስት ቤተ

ክርስቲያን ፣ ስለተጎጂዎቹ ልጆችዋ የመንግሥትን ቸልተኝነት ፊት ለፊት ያጋለጡ፣ ጊዜ የሰጠውን አጥፊ ሳይፈሩ በክፉ ቀን ከቤተ ክርስቲያን ጎን የቆሙ ፣ ሳይሳቀቁ ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን የጮኹ የቤተ ክርስቲያን የቁርጥ ቀን ልጆች አርዓያዎቻችን ናቸው:: በተለይም ነገን እንዴት መኖር እንዳለብን አሳይተውናልና የመንፈስ ጥንካሬያቸውን፣ መንፈሳዊ የዓላማ ጽናታቸውን አርአያ ልናደርገው ይገባል::

የጠላትን ዛቻና ጥፋት ሳይሳቀቁ ያጋለጡ የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ከምእመኑ እስከ ቅዱስ ፓትርያርኩ ለአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሕልውና ከፊት ቆመው ጮኸዋል:: በቃል ብቻ ሳይሆን ጥፋት በደረሰባቸው ቦታዎች ተገኝተው የምእመኑን ኀዘን ተካፍለዋል፣ ያላቸውንም በመስጠት ብርታት እና ጉልበት ሆነዋቸዋል:: ስለቤተ ክርስቲያን መሥዋዕትነትን የከፈሉ ምእመናንን፤ ቤተ ክርስቲያን ለዘላለም ታስባቸው ዘንድ ‹‹የቤተ ክርስቲያን የሰማዕታት ቀን›› ብለው ሰይመውላቸዋል:: ዛሬ መልካም ዛፍን ተክለው የነገዋ ቤተ ክርስቲያን ፍሬዋ እንዲበዛ አድርገዋል:: በየቦታው ሲመቱት የሚጠብቅ ክርስቲያንን አንጸዋል፣ የቤተ ክርስቲያን ልጆች እንዴት መኖር እንዳለብን ክርስትናን በተግባር አሳይተውናልና በክብር ሊዘከሩ ይገባል::

ቦታና ጊዜ ሳይገድባቸው ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጀሮአቸውን የሰጡ፣ እጃቸውን የዘረጉ ከውስጥና ከውጭ ያሉ የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች፣ ማኅበራት፣ ድርጅቶች የነበራቸውን ተሳትፎ በቀላሉ ማየት አይቻልም፤ ለቤተ ክርስቲያን ብዙ ነገር ማለት ነውና:: በመከራ ውስጥ ያለፈችውን ቤተ ክርስቲያንን እና ምእመናንዋን ለመታደግ ገንዘባቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ዕውቀታቸውን ሳይሰስቱ በመስጠት ከሕመሟ እንድትፈወስ፣ ከድካሟ እንድትበረታ፣ በጽናቷ እንድትቀጥል በማድረግ ለቀረው ምእመን የቤት ሥራ ሰጥተዋል::

ቤተ ክርስቲያናችን ላይ የተጋረጠውን መከራ ፊት ለፊት በመናገር ፣ በማስጠንቀቅ እንዲሁም ምእመናኑን በማጽናናት አባቶቻችን ያሳዩት ቁርጠኝነት ለቤተ ክርስቲያን ትልቅ ብርታት ሆኗታል:: በቦታው ላይ በመገኘት ለምእመናን ያሳዩት አባታዊ ፍቅር እና ምክር የመልካም እረኝነትን ተግባር የገለጠ ነውና ሳይታሰብ መታለፍ የለበትም:: ታላላቅ ጉባኤያትን በማዘጋጀትና በቦታው ላይ በመገኘት ለምእመናኑ አባታዊ ምክር በመስጠት ፣ በመባረክ የቤተ ክርስቲያንን ተልዕኮ የተወጡ አባቶቻችን፣ በቃለ ወንጌሉ ፣ በዝማሬ ሲያጽናኑ የነበሩ ወንድሞቻችን እና እኅቶቻችን ለቤተ ክርስቲያን ባሳዩት ፍቅር ልክ ሊታሰቡ ይገባል::

በፈረሰው በኩል በመቆም ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቷ እንዳይቋረጥ ባጠቃላይ ምእመንዋ እንዳይበተንና፣ እንዳይጠፋ ባለበት ጸንቶ እንዲቆም የታገሉ ሁሉ ምስጋና ይገባቸዋል:: በተለይም የጥቃቱ ሰለባ የነበሩቱ ስአንዲትዋ ቤተ ክርስቲያን ተላልፎ መስጠት እየሞቱ መኖር እየጠፉ መብዛትን አስተምረውናል:: በሁሉም መንገድ ከእናት ቤተ ክርስቲያናቸው ጋር አብረው መከራውን የተቀበሉ፣ የቁርጥ ቀን ልጆች ታላቅ መልእክት አስተላልፈውልናል::

# ''የመንታ እናት ተንጋላ ትሞት''

በዲ/ን አሻግሬ አምጤ

ቤተ ክርስቲያን የሰላም በር ብትሆንም በየጊዜው በልዩ ልዩ ምክንያት በተከሠተ ጦርነት ስትለበለብ ኖራለች። ጦርነት አውዳሚ መሆኑን ተረድታ ክፉዎች በጥፋት ቀጥለው ዘለዓለማዊ ቤታቸውን እንዳያጡ ትጸልያለች። ጸሎቷም በዓለም ላይ አማናዊው ሰላም ይሰፍን ዘንድ ነው። ጦርነት በተከሠተ ጊዜ ግን ተዋጊዎች በአንድ በኩል ከለላ ለማግኘት በሌላ በኩል ደግሞ ሆን ብለው ለማስጠቃት ቤተ ክርስቲያንን ይጠጋታል።

ከውጭ ወራሪ ጋር የሚደረግ ጦርነት ከሆነ ቤተ ክርስቲያን እንደ አገር ለትውልድ ሥነ ልቡና መገንቢያ ተደርጋ ስለምትታሰብ በጦርነት ስትለበለብ ኖራለች። በመጀመሪያው ወረራው ግማሽ ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሽንፈትን ተከናንቦ የፈረጠጠው ፋሽስት ኢጣሊያ ለሁለተኛው ጊዜ አገራችንን ለመውረር ሲያስብ ለኢትዮጵያውያን ጀግንነት ምክንያቱን አጥንቶ ቤተክርስቲያን መሆኗን ደረሰበት። ከጥናቱ በመነሣትም ቤተክርስቲያንን አንዷ የጥቃት ዒላማ እንድትሆን አድርጐ ክርስቲያኖችንና አብያተ ክርስቲያንን አወደመ። የአንድ እናት ልጆች በአንድ በኩል አገርን ለመታደግ በሌላ በኩል ደግሞ ለማፍረስ ከመጣው ፋሽስት ጋር በመወገን ኢትዮጵያን አወደሙ። የጦርነት ፍጻሜው እንዲህ ነው።

በዚህ ምክንያትም ፋሽስት ኢጣሊያ ከደብረ ሊባኖስ ገዳም ብቻ ከ፳፪ እስከ ፴፻፫፻፪ የሚደርሱ መነኰሳትን እንደፈጁ፣ ወደ ሞቃዲሾ እንዳጋዙና ታስረው እንዲሠቃዩ እንዳደረገ ኢያን ካምቤል የተባለ ጸሐፊ “The Masackre of Debre Libanose” በተሰኘው መጽሐፉ ገልጧል። በየዘመናቱ የተነሡ ወራሪዎችና ለጦርነት የተሰለፉ አካላት ቤተክርስቲያንን ለሁለት ነገር ሲጠቀሙባት ኖረዋል። የመጀመሪያው ክርስቲያን መስለው ሕዝበ ክርስቲያኑን ሰብስበው ለጦርነት ለመማገድ ሲሆን ሁለተኛው በጦርነት የሚሸነፉ ከሆነ ጠላት ደፍሮ ስለማይገባ ጊዜ መግዣ እናደርገዋለን፣ ጨክኖ ተኩስ ከከፈተም ከጦርነት ቀጠና ነፃ መሆን ባለባቸው ቤተ እምነቶች ላይ ጥቃት ፈጸመ ብለን ለዓለም ኅብረተሰብ ለማሳጣት ይመቸናል ብለው የሚፈጽሙት እኩይ ድርጊት ነው።

በአሁኑ ጊዜ እየተፈጸመ ያለው ጦርነትም የአንድ አገር ልጆች በመሆኑ በሁለቱም ወገን ለጦርነት የተሰለፉ አካላት አብያተ ክርስቲያናትን፣ አቅመ ደካሞችን፣ ሕፃናትንና ሴቶችን ዒላማ ከማድረግ መቆጠብ እንደሚኖርባቸው ዓለም አቀፍ ተቋማት እየገለጡ ነው። ቤተ ክርስቲያንን ተገን አድርገው ሌላውን ለማጥቃት የሚፈልጉ አካላትም ሆኑ ጠላት የሚሉት በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ መስፈሩን እያወቀ ጦርነት የከፈተ በዓለማዊ ሕግም፣ በሞራልም የሚያስጠይቅ ነው።

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም “ችግር ሁልጊዜ አንዳንድ መልካም ነገሮችን ይዞ ይመጣል፤ የዘመኑ ወረርሽኝም በእኔ አስተያየት ሁለት ጥሩ ነገሮችን አስከትሏል፤ አንዱና ዋናው ከጃንሆይ በኋላ ተሽሮ የነበረው እግዚአብሔርን መልሶ በቦታው ማስቀመጡና በየመገኛዎች የእግዚአብሔርን ስም ማንሣት ተለመደ፤ ይህ ትልቅ ንቃት ነው፤ እግዚአብሔር ሁሌም በመንበሩ ላይ ነው፤ አይነቃነቅም፤ ሁለተኛው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተረስታ ወደጓዳ ተደብቃ ነበር፤ ዛሬ ጉልበትዋ በሙሉ ባይሆንም ታየ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዝናዋ አልተነገረም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያለበትን ውለታ ገና በትክክልና በዝርዝር የተናገረው የለም፤ እንደተዳፈነ ነው፤ ቤተ ክርስቲያኒቱን ተደግፈው የሚወጡ ሁሉ በሥልጣኑ ጣዕምና ሙቀት እዚያው ቀልጠው ይቀራሉ፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለውነተኛ ተማሪዎች የሊቅነት ማዕርግ የሚያሰጣቸው ነው፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የትምህርት ሚኒስቴር ነበረች፤ የበጎ አድራጎት ሚኒስቴር ነበረች፤ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ነበረች፤ የባህልና የቅርስ ጥበቃ ሚኒስቴር ነበረች … በዛሬው ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ

ክርስቲያን የተማሩ ሰዎች አላጣችም፤ እንደ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ያለው እንኳን ደፍሮ ጉልበተኞችን መጋፈጥ አልቻሉም” በማለት የገለጧት ቤተ ክርስቲያን አሁንም ለአደጋ ተጋልጣለች። ክርስቲያኖች እርስ በርስ እየተፋጀን መተላለቃችን አገራችንንና ቤተ ክርስቲያናችንን ይጎዳል እንጂ አይጠቅምም። ለአደጋ የሚጋለጡት ክርስቲያኖች ናቸው። ክርስቲያኖች ተሰደው የሚሔዱትም በእምነት ወደ ማይመስሏቸው አካባቢዎች በመሆኑ ችግሩን ይበልጥ ውስብስብ ያደርገዋል።

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዝናዋ አልተነገረም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያለበትን ውለታ ገና በትክክልና በዝርዝር የተናገረው የለም፤ እንደተዳፈነ ነው፤ ቤተ ክርስቲያኒቱን ተደግፈው የሚወጡ ሁሉ በሥልጣኑ ጣዕምና ሙቀት እዚያው ቀልጠው ይቀራሉ፤

ኅዳር ፲፭ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም. ኢሰመኮ በሰጠው መግለጫ መሠረት ትግራይ ክልል ማይካድራ በተባለች ከተማ በተፈጸመው የንጹሐን ዜጎች ጭፍጨፋ ብዙዎች ግፍና ጭካኔ በተሞላበት ድርጊት በጅምላ ተገለዋል። መግለጫው የተጎዱትን ማቋቋም እና የአጥፊዎችን ተጠያቂነት ማረጋገጥ እንደሚገባ ገልጦ “በትግራይ ክልል ምዕራባዊ ዞን በምትገኘው የማይካድራ ከተማ ጥቅምት ፴ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም. በወቅቱ በሥልጣን ላይ በነበረው የአካባቢው መስተዳድር የፀጥታ መዋቅርና ሳምሪ በተባለ ኢ-መደበኛ የወጣቶች ቡድን የተፈጸመው ጥቃት፤ ግድያ፣ ጉዳትና ውድመት፤ ጠቅላላ ድርጊቱና ውጤቱ ግፍና ጭካኔ የተሞላበት በንጹሐን ሰዎች ላይ የተፈጸመ የጭፍጨፋ ወንጀል (atrocious crime of massacre against civilians) መሆኑን አስታውቋል። መታወቅ የሚኖርበትም ለመግደል ከተሰማሩት ብዙዎቹ፣ ከሞቱትም ብዙዎቹ ክርስቲያኖች ሊሆኑ የሚችሉ መሆናቸው ነው። ጦርነቱ በሕንፃ ቤተክርስቲያን፣ በቅርሶች፣ በአቅመ ደካሞች ላይ ተጨማሪ ጉዳት እንዳያደርስ መጠንቀቅ ይገባል። እንደ ኮሚሽኑ መግለጫ ከኅዳር ፭ እስከ ኅዳር ፱ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም. ድረስ በማይካድራ ከተማ እንዲሁም በአብርሀጅራ፣ በሳንጃ፣ በዳንሻ፣ በሁመራ እና በጐንደር ከተማ ተዘዋውሮ ባደረገው ምርመራ የደረሰበት ግኝት ነው።

ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት በሰብአዊነት ላይ የተፈጸመ ወንጀል (crimes against humanity) እና የጦር ወንጀል (war crime) ሊሆን እንደሚችል ገልጧል። የኢሰመኮ ዋና ኮሚሽነር ዳንኤል በቀለ (ዶ/ር) “በማይካድራ ከተማ በአነስተኛ ጽንፈኛ ቡድን የተፈጸመው በብሔር ማንነት ላይ የተመሠረተ እጅግ ዘግናኝ ኢ-ሰብአዊ ወንጀል ልብ ሰባሪ ቢሆንም፣ በአንጻሩ ኢትዮጵያውያን በብሔር ሳይለያዩ አንዱ የሌላው ጠባቂ ሆነው መታየታቸው ልብ ይጠግናል፤ ለወደፊቱም በሰላም አብሮ መኖርም ተስፋ ይሰጣል። የተጐዱ ሰዎችን እና አካባቢዎችን መልሶ ከማቋቋምና ከመጠገን በተጨማሪ፣ በዚህ ከባድ የሰብአዊ መብቶች ወንጀል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተሳተፉ በየደረጃው ያሉ ጥፋተኞችን በሕግ ፊት ተጠያቂነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል” ብለዋል። እንግዲህ ይህ ሁሉ የሚያሳየን ኢትዮጵያውያን ጠበብ ካደረግነው ደግሞ ክርስቲያኖች እርስ በርስ እየተፋጀን መሆኑን ነው። ድርጊቱ ቤተ ክርስቲያንን የማይስማሙ ‹‹የመንታ እናት ተንጋላ ትሞት›› የሚያስብል ነው።

# “በውጪው ዓለም ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች ሳይሆን ተስፋፋች እላለሁ”

*-መልአከ ገነት በለጠ ይረፉ*

***ክፍል ሁለት***



መልአከ ገነት በለጠ ይረፉ

በመጽሐፈ ሲራክ

*የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል። ቀጣዩንና የመጨረሻውን ክፍል ደግሞ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።*

***ስምዐ ጽድቅ፦*** የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አንድነት መምጣቱ መልካም ነገር ሆኖ ሳለ ምናልባት በውጪው ሀገር ለክርስትናው መስፋፋት መከፋፈሉን እንደ በጎ ልናየው እንችል ይሆን?

***መልአከ ገነት በለጠ ይረፉ፦*** በምንም አይነት መለያየትን እንደ መልካም ነገር ልናየው አንችልም። በተለይ የቤተ ክርስቲያን ሲሆን ደግሞ መለያየት ክፉ ነው ብዙ ጠባሳ ጥሎ ንፁሐንንም አቁስሎ ያልፋል። በነበረው መከፋፈል የተነሳ በዓለም ላይ መሥራት የሚገባንን መንፈሳዊ ሥራ ሳንሠራ ቀርተናል፤ አገልግሎቱንም ጎድተናል፤ ሕዝቡን ለመናፍቃን ገብረናል፤ ብዙ ነገር አበላሽተናል።

የወላጆች መከፋፈል ለልጆች፤ የመሪዎችም መከፋፈል ለተመሪዎች ምን ያህል ችግር መሆኑ ይታወቃል። እንግዲህ ይህንን ስናስብ መለያየትን ልንጠየፈው ያስፈልጋል። ይኽ ደግሞ አጋጥሞን አልፏል፤ በታሪክ አጋጣሚ ይህንን አስተናግደናል፤ የምንወደውን ትተን የምንጠላውን ሆነናል፤ በወቅቱ በፓለቲካም ይሁን በቅዱስ ሲኖዶስ በዘርም ይሁን በሥልጣን ተበታትነን ሳለን ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ስላገኘን ይህንን ነገር እግዚአብሔር ለበጎ አድርጎት ይሆን? ብለን እንጠይቃለን ሰዎች ነንና እንዲህም እናስባለን ደግሞ እንመለስና እንዴት በእግዚአብሔር ፊት መለያየትን ለበጎ እንላለን? የሚል ሐሳብም ይመጣል።

በሀገራችን ጥንት ቤተ ክርስቲያን ይቋቋም የነበረው ያለው ቤተ ክርስቲያን ለምእመናን ሲርቃቸው፣ ወንዝ እየሞላ ሲያስቸግራቸው፣ ሕፃን ታቅፈው ለማስጠመቅ፣ ሰው ሞቶባቸው ለቀብር ሲርቃቸው፣ በአካባቢያቸው ደብር እንዲኖራቸው በሚል ቅን ሐሳብ በስምምነት ነው እንጂ ተጣልቶና ተኳርፎ ተለያይቶ የሚሆን አይደለም በውጪ ሀገር ግን ሁሉም ባይሆኑም አንዳንድ ቦታ ያሉት የመለያየት ውጤቶች ናቸው።

አሁን የጥንቱ አንድነት ተመልሷል፣ ቅዱስ ሲኖዶስ አንድ ሆኗል፣ ቀደም ሲልም ልዩነቱ የጀመረው ከላይ ነበር አሁንም ከላይ ተስተካክሏል በተፈጠረው ልዩነት ስናዝን የነበርነው ካህናትና ምእመናንንም አሁን አንድ በመሆናችን ደስተኞች ነን።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ቤተ ክርስቲያን በውጪው ዓለም ይበልጥ እንድትስፋፋ አሁን ምን እየተደረገ ነው ያለው?

***መልአከ ገነት በለጠ፦*** የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ለማስፋፋትና ለማጠናከር በየደረጃው ብዙ ጥረት ይደረጋል:: በተለይ በአንዳንድ አድባራት ስብከተ ወንጌልን ለማዳረስ ወጣቶችንም ለማደራጀት እየተሠራ ነው:: በውጪ ሀገር ተወልደው ያደጉ ልጆች ሃይማኖታቸውን እንዲያውቁ፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን እንዲጠብቁ በሚገባቸው ቋንቋ እንዲማሩ ይደረጋል:: ብዙ አድባራት ለሕፃናት፣ ለማዕከላውያንና ለወጣቶች ለአዋቂዎች ጭምር ሥርዓተ ትምህርት ቀርፀው ያስተምራሉ ለምሳሌ የእኔን ደብር ብጠቅስ በየሳምንቱ ቅዳሜና እሑድ ለሕፃናት፣ ለወጣቶችና ለአዋቂዎች በየደረጃቸው የሃይማኖት ትምህርት፣ የመዝሙር ጥናት እንዲሁም የቋንቋ ትምህርት ይሰጣል:: ብዙዎችም በዚህ ተጠቅመዋል በማስተማርም የሚያገለግሉ አሉ በርካታ ዲያቆናትም ያፈራነው ከዚያው ነው:: በዚህ አጋጣሚ በርካታ ዲያቆናትን በማስተማር ከፍተኛውን ሥራ የሠሩትን የደብራችን ካህን መጋቤ ሃይማኖት ዘለዓለም ጽጌን፤ ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር ተተኪ የሆኑትን ወጣቶችንና ሕፃናትንም ጭምር በማስተማር የሚደክሙትን ወንድሞችና እህቶች ላመሰግን እወዳለሁ ከእኔ ይልቅ እነርሱ ይበረታሉ:: ቤተ ክርስቲያንም አለች እየሠራች ነው ማለት የሚቻለው ሕፃናትን ማዕከላውያንና ወጣቶችን ይዛ ለነገ ተረካቢ እንዲሆኑ ከአስተማረች ነው::

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለው አብሮ የመሥራት፣ ግንኙነቱና መተጋገዙ ምን ይመስላል?

***መልአከ ገነት በለጠ፦*** በውጪ ዓለም እንደ ሀገር ውስጥ አብያተ ክርስቲያናቱ በቅርብ ርቀት የሚገኙ አይደሉም:: ብዙዎቹ የሚገኙት በግዛት ደረጃ ነው ለምሳሌ እንደ ኮሎምቦስ፣ ቺጋጎ ባሉ ግዛቶች ውስጥ በርካታ አድባራት ይገኛሉ:: በሌላው ግዛት ደግሞ አንድ ደብር ብቻ ይሆናል:: ለምሳሌ በዚሁ ሀገረ ስብከት ሥር ያሉ ሌሎች ግዛቶች አንዳንድ ቤተ ክርስቲያን ነው ያላቸው:: እና በጋራ ለማገልገል ሁልጊዜ የመገናኘቱ ነገር ከባድ ቢሆንም በበዓላት፣ በንግሥ ጊዜ የአንዱ ደብር ካህናትና ምእመናን ወደ ሌላው ደብር ጉዞ በማድረግ ከዋዜማው እስከ ክብረ በዓሉ ድረስ ማኅሌቱን፣ ቅዳሴውን ጠቅላላ አገልግሎቱን በጋራ ይሰጣሉ::

አንዱ ያለ አንዱ ለብቻው አያከብርም ለዚህም ሲባል ብዙውን ጊዜ በዓላት የሚከበሩበት ቀዳሚት ሰንበት ነው:: እንዲህ የሚደረገው በዕለተ እሑድ በየደብራቸው አገልግሎት ስለአለ ሲሆን ከሰኞ እስከ ዓርብ ደግሞ ሕዝቡ በሥራ ላይ ስለሆነ ነው:: በሕብረት በአንድነት ማገልገሉ እያደገ መጥቷል በተለይ መለያየቱ ቀርቶ ቤተ ክርስቲያን አንድ ከሆነችበት ቀን ጀምሮ እግዚአብሔር ይመስገን መቀራረቡ አለ:: በእርግጥ ቅዱስ ሲኖዶስ በዚህ በኩል ብዙ ሥራ ይጠበቅበታል እርቅና አንድነት በሲኖዶስ ደረጃ ተፈፅሞ መቅረት የለበትም ወደ ታች ወደ ካህናቱ ብሎም ወደ ሕዝቡ ሊወርድ ይገባል:: ቀደም ሲል ካህናትና ምእመናን በነበረው መከፋፈል ለየብቻ ቆይተዋል እርቁ ሲመጣ ግን አባቶች በአንድነት ሲሆኑ ያንን መልሰው ወደ ሕዝቡ ማምጣት ነበረባቸው:: ይህንን ሐሳብ ያኔ በእርቁ ሰነድ ላይ አስቀምጠውታል ተናግረውታልም እኛም እንጠብቅ ነበረ:: በእርግጥ ያንንም ሳንጠብቅ እኛ ካህናቱ እርስ በርስ መነጋገር አንድነቱን፣ ሕብረቱን፣ መቀራረቡን እየፈጠርን ስለሆነ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አንዲት ሆናለችና እግዚአብሔር ይመስገን::

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በጋብቻ ሕግ ተወስነው የሚኖሩ ካህን ነዎትና እስኪ ስለ ቤተሰብዎ ይንገሩን?

***መልአከ ገነት በለጠ፦*** እውነት ነው በቅዱስ ጋብቻ ተወስኜ በትዳር የምኖር ካህን ነኝ:: ከባለቤቴ ጋር ያፈራናቸው አራት ልጆች አሉን:: ስማቸውም ዲያቆን ተዋሕዶ በለጠ፣ ሜላተ ወርቅ በለጠ፣ ወንጌል በለጠ እና ኖላዊ በለጠ ይባላሉ:: ባለቤቴ እጅግ የተባረከችና የተወደደች ሚስት ናት:: ስሟ አብነት ነጋሽ ይባላል:: ለመንፈሳዊ አገልግሎቴ መሳካት ትልቅ ኃይልና ብርታት የምትሰጠኝ ልዩ ስጦታዬ በረከቴ ናት:: “ደግ ሚስትን ያገኘ ሞገስን አገኘ ፥ ከእግዚአብሔርም ደስታን ተቀበለ::” ምሳ ፲፰፥፳፪ እንዲል እግዚአብሔር በጎደለኝ በኩል ሊሞላልኝ እርሷን

መርጦ እንደሰጠኝ አምናለሁ። ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በአለኝ ሞያና በተሰጠኝ ፀጋ በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር ተዘዋውሬ እንዳገለግል፣ አርአያ ክህነቴን እንድጠብቅ በማድረግ በኩል የእርስዋ ድርሻ ትልቅ ነው።

ጋብቻ ከመሠረትን ቆየን ሃያ አምስተኛ ዓመት የብር ኢዮቤልዩ አክብረናል፤ አሁን ሃያ ሰባተኛ ዓመት ሊሆነን ነው። ባለቤቴ በሕፃንነቷ የጀመረችው አገልግሎት ዛሬም እናት ሆና በሰንበት ት/ቤት ልጆቻችንን ይዛ እያገለገለች ትገኛለች። ሁሉም ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አይለዩም በየደረጃቸው ያገለግላሉ።

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** በአገልግሎት ዘመንዎ ውስጥ ገጠመኝ የሚሉት መልካምና መጥፎ ገጠመኝ ካለ ቢነግሩን

***መልአከ ገነት በለጠ፡-*** እውነት ነው ማግኘትና ማጣት፣ ማዘንና መደሰት፣ መሾምና መሻር እነዚህ ሁለቱ በሰው ልጅ ሕይወት ላይ ሲፈራረቁ የሚኖሩ ናቸው። የሰው እድሜው መንፈቁ ለክብር መንፈቁ ለኃሣር ግማሽ ዕድሜው ለክብር ግማሹ ደግሞ ለመከራ ነው ሁልጊዜ አይደሰትም ሁልጊዜ ደግሞ እያዘነ አይኖርም።

ከላይ እንደገለጥኩት እኔ በብዙ አድባራት በኃላፊነት ለብዙ ዓመታት አገልግያለሁ የእግዚአብሔር ቸርነት የቅዱሳን ጸሎት እየረዳኝ በሰላም በፍቅር በምስጋና በሽልማት ነው የኖርኩት። በዝውውር ተነስቼ ወደ ሌላ ደብር ስሔድ እንኳ "ይመለስልን" እየተባለ ነው የኖርኩት "መልካም ሀብት ሁሉ፥ ፍጹም ዕድልም ሁሉ ከላይ ነው፤. . ." ያዕ ፩፥፲፯ እንዲል መጽሐፉ ይህ ከእኔ የተነሳ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ የተደረገ ነው።

መንፈሳዊ አገልግሎት በፍቅር ከአልሆነ ምንም ዋጋ እንደሌለው አምናለሁ፤ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም መኖር እወዳለሁ፤ እኔ ዝቅ ብዬ ሌላው ከፍ ቢል ደስ ይለኛል። ተበድዬም እንኳን ስለፍቅር ይቅርታ እጠይቃለሁ ቅዱስ ጳውሎስ ፩ኛ ቆሮ ፰ ፥ ፲፫ "ነገር ግን በመብል ምክንያት ወንድሜ የሚሰናከል ከሆነ ወንድሜን እንዳላሰናክል ለዘለዓለም ሥጋን አልበላም።" እንዳለው ሰውን አስቀይሜ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አልችልምና የእኔ ጥቅምና መብት መሆኑን እንኳ እያወኩ በዝምታ አልፈዋለሁ። ባለማወቅ አይደለም ፤በሞኝነትም አይደለም እግዚአብሔር ለእኔ ያለውን እንደሚያደርግልኝ ስለማምን ነው። ስለዚህ ብዙ ችግር አጋጥሞኝ አያውቅም። ምንም ነገር ፈተናና ችግር አጋጥሞኝ አያውቅም ማለት ግን አይደለም በእኔ ላይ የደረሰውን ያጋጠመውን (ያሳዘነኝን) ሳይሆን ለእኔ የደረሰውንና የሆነውን የእግዚአብሔርን አስገራሚ የሆነውን ድንቅ ነገር ሳስብ መልካሙ ነገር ሚዛን ይደፋልና እንዲሁ ስለአደረገልኝ ነገር ተመስገን እላለሁ።

**ጥንት ቤተ ክርስቲያን ይቋቋም የነበረው ያለው ቤተ ክርስቲያን ለምእመናን ሲርቃቸው፣ ወንዝ እየሞላ ሲያስቸግራቸው፣ ሕፃን ታቅፈው ለማስጠመቅ፣ ሰው ሞቶባቸው ለቀብር ሲርቃቸው፣ በአካባቢያቸው ደብር እንዲኖራቸው በሚል ቅን ሐሳብ በስምምነት ነው**

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** እንደሚያውቁት በሀገር ቤት ያለችው ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ዛሬ አይነቱ ብዙ የሆነ ጥቃት እየተፈፀመባት ነውና እርስዎ ስለዚህ ምን ይላሉ ?

***መልአከ ገነት በለጠ፡-*** በቅድሚያ በቅድስት ቤተ ክርስቲያንና በክርስቲያኖች ላይ እየደረሰባቸው በሚገኘው ጥቃት ሞትና ስደት ከፍተኛ ኃዘን ይሰማኛል በክርስትናቸው የተነሳ ለሞቱት ወገኖቼ ነፍሳቸውን ይማር እላለሁ።

በሰው ሀገር በባእድ ምድር የምትኖር ቤተ ክርስቲያን ክብሯና መብቷ ተጠብቆ በነፃነት ትኖራለች፤ አገልግሎቷንም በሚገባ እየሰጠች ትገኛለች በተቃራኒው ግን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በገዛ ሀገርዋ ላይ ስደተኛ እየሆነች ነው:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ባለውለታ ናት:: ታሪክ ሠርታና አቆይታ ያስረከበች፤ እውቀትን፣ ፍቅር አንድነትን ያስተማረች፤ ጠላት ወራሪን የመከተች ለሀገሪቱ ዳር ድንበር የዘመተች ብዙ ውለታ ያላት ቤተ ክርስቲያን ናት:: መጽሐፍ ቅዱስ" በግብፅ ዮሴፍን ያላወቀ ሌላ ንጉሥ ተነሣ "ዘፀ ፩ ፥፰ እንዲል በሀገራችን የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ታሪክና ውለታ የማያውቁ ሰዎች ተነስተዋል:: አንዳንዶች ያለ ስሟ ስም ያለ ግብሯ ግብር ሲሰጧት ይሰማሉ፣ ይታያሉ :: ምዕመናንን የሚያሳድዱ፣ በጭካኔ የሚያርዱ፣ እሳት የሚያነዱ አሉ:: የምትጠፋ መስሏቸው ብዙ እየጣሩ ነው ፤ የጥምቀትና የደመራን በዓል ማክበሪያ ቦታዎቿን ሳይቀር እየነጠቋት ነው በርግጥ ሊያጠፏት የሚጥሩት ይጠፋሉ እንጂ ቤተ ክርስቲያን ከቶም አትጠፋም የትላንት ታሪክ የሚነግረን ይኽን ሀቅ ነውና::

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ይኽ ሁሉ ግፍ የሚደርስባት በደል ተገኝቶባት አይደለም ምናልባት በውስጥዋ የምኖረው እኔ ተሳስቼ አጠፋ ይሆናል እንጂ እርስዋ የምትሳሳት አይደለችም:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን ከኢትዮጵያ ለይቶ ማየት አይቻልም የማይነጣጠሉ ናቸውና:: የሌሎች እምነት ተከታዮች ወደ ሀገራችን ሲመጡ "ግቡ ቤት የእንግዳ ነው" ብላ እጇን ዘርግታ የተቀበለችና ሀገር ያለማመደች ዛሬም ቢሆን "ዕቀብ ሕዝባ ወሠራዊታ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ " እያለች ለሀገር ለወገን ሰላምን ፍቅር አንድነትን ስጥልን ብላ የምትጸልይ ናት::

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ተከብራ የኖረች ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ሆና ማየት እጅግ ያሳዝናል:: በብዙ ቦታ ካህናት ምእመናን ስማቸው እየታየ አድራሻቸውም እየተመዘገበ ተገደሉ፣ ተፈናቀሉ፣ አድባራቱም ተቃጠሉ፣ ሀብት ንብረታቸው እንዲወድም ተደረገ ሲባል ኃዘን ይሰማኛል፤ ልቤ ይሰበራል:: ይህ ችግር ወደፊት እንዳይቀጥል ከላይ ከቅዱስ ሲኖዶስ በሳልና ጠንካራ የሆነ ውሳኔና አመራር ይጠበቃል:: ቤተ ክርስቲያን የሰውና የታሪክ የሀብትም ድሀ አይደለችም በመንፈሳዊም ሆነ በዘመናዊ እውቀት የበሰሉ ብዙዎች አሉአት እነርሱን ወደ ኃላፊነት ማቅረብ ካህናቱንና ምእመናኑም በሕብረት በአንድነት መምራት ያስፈልጋል:: ከእኛም ከካህናትና ከምእመናንም የሚጠበቅ ነገር አለ ከመለያየት ከመከፋፈል ርቀን ለአንዲት ቤተ ክርስቲያናችን በአንድነት መቆም ይገባናል::

> **ጋብቻ ከመሠረትን ቆየን ሃያ አምስተኛ ዓመት የብር ኢዮቤልዩ አክብረናል፤ አሁን ሃያ ሰባተኛ ዓመት ሊሆነን ነው:: ባለቤቴ በሕፃንነቷ የጀመረችው አገልግሎት ዛሬም እናት ሆና በሰንበት ት/ቤት ልጆቻችንን ይዛ እያገለገለች ትገኛለች:: ሁሉም ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አይለዩም በየደረጃቸው ያገለግላሉ::**

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በሰሜን አሜሪካ የኦሃዮና አካባቢው አህጉረ ስብከትን ወክለው የ፴፱ኛውን ዓለም አቀፍ መንፈሳዊ ሰበካ ጉባኤ ለመካፈል ነው የመጡት ከዚህ ጉባኤ ምን አገኙ?

***መልአከ ገነት በለጠ፦*** እውነት ነው ዘንድሮ ወደ ኢትዮጵያ የመጣሁት ሀገረ ስብከቴን ወክዬ በ፴፱ኛው ዙር ዓለም አቀፍ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ ለመካፈል ነው:: በዚህ ታላቅ ጉባኤ ላይ ሁለቱ ቅዱሳን ፓትርያርኮች፣ሁሉም ሊቃነ ጳጳሳት፣ የመምሪያ ኃላፊዎች፣የሁሉም አህጉረ

ስብከቶች ሥራ አስኪያጆችና የሥራ አመራሮች የአዲስ አበባ ገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎችና ተወካዮች ተገኝተውበታል፡፡ ሁሉም የቤተ ክርስቲያንን ጥሪ ሰምቶና አክብሮ በመገኘቱ ደስ ብሎኛል ቤተ ክርስቲያን ስትጣራ መስማትና አቤት ብሎ መገኘት ጥሩ ነገር ነው እኔም የዚህ ታላቅ ጉባኤ ተካፋይ በመሆኔ በጣም ደስተኛ ነኝ ፡፡

**ቤተ ክርስቲያን የሰውና የታሪክ የሀብትም ድሀ አደለችም በመንፈሳዊም ሆነ በዘመናዊ እውቀት የበሰሉ ብዙዎች አሉአት እነርሱን ወደ ኃላፊነት ማቅረብ ካህናቱንና ምእመናኑም በሕብረት በአንድነት መምራት ያስፈልጋል። ከእኛም ከካህናትና ከምእመናንም የሚጠበቅ ነገር አለ ከመለያየት ከመከፋፈል ርቀን ለአንዲት ቤተ ክርስቲያናችን በአንድነት መቆም ይገባናል።**

በሌላ በኩል ዘመኑ ዘመነ ኮረና (COVID-፲፱ ) ስለሆነ ለሁሉም ነገር በተለይ ለመሰብሰብ ተቀራርቦም ለመነጋገር አስቸጋሪ ስለሆነ ያስፈራል የስጨንቃል ይህንን አውቃለሁ፤ ቢሆንም ወደ ስብሰባው ስመጣ ብዙ ነገር ተስፋ አድርጌ ነው የመጣሁት፡፡ የምጠብቀው ብዙ ነገር ነበር ከሞላ ጎደል መልካም ነበር ወቅታዊውን የቤተ ክርስቲያንን ችግር፣ የክርስቲያኖችን ነገር በሚመለከት ሰፊ ጊዜ የሚሰጠውና ውይይት የሚደረግበት ሰፊ ክፍለ ጊዜ ይኖራል፤ ከስብሰባው ተካፋዮችም ልዩ ልዩ ሐሳቦች ይቀርባሉ እኔም የማውቀውን የሰማሁትንና ያየሁትን ችግርና የመፍትሔ ሐሳብ ጨምሬ እናገራለሁ ብዬ ነበር፡፡ ነገር ግን የውይይት ጊዜ አልነበረም በዚህ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ ለመገኘት ከመላው ዓለም የሚመለከታቸው ተወካዮች ተገኝተዋል፤ የጉባኤው መሪና አስተባባሪ ጠቅላይ ቤተ ክህነቱ ለጉባኤው መዘጋጀት ብዙ ደክሟል፤ እያንዳንዱ ሀገረ ስብከት ብዙ የገንዘብ ወጪ አድርጓል፤ ተሰብሳቢዎች ሥራቸውን በመተው ተገኝተዋል፤ ምእመናንም ከዚህ ጉባኤ ብዙ ይጠብቃሉ፡፡

በአጠቃላይ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዘመን በውስጥና በውጪ ለገጠማት ችግር የመፍትሔ አቅጣጫ ይነገርበታል፣ ይወሰንበታል ለቅዱስ ሲኖዶስም ትልቅ ግብአት ይሆናል ብዬ ነበር፡፡ ለሁለት ቀናት የሁሉንም አህጉረ ስብከት ሪፓርት ሰማን ከውጪ ሀገርም እንዲሁ አደመጥን እግዚአብሔር ይመስገን እኔም ተራ ደርሶኝ የሀገረ ስብከቴን ሪፖርት በንባብ ለጉባኤው አቀረብኩ፡፡ በእርግጥ የውይይይት ጊዜ ሳይሰጥና ሐሳባችንን ሳናካፍል ስብሰባው ቢፈጸምም ከቀረበው ሪፖርት በመነሳት በጉባኤው ማጠቃለያ የቀረበው የአቋም መግለጫ የሁሉንም ሐሳብ የያዘና ችግሮችን አንስቶ የመፍትሔ ሐሳብ ለቅዱስ ሲኖዶስ ያመላከተ ስለሆነ አሁንም የመጨረሻው አካል የሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ የዚህን ታላቅ ጉባኤ ውሳኔ ተመልክቶ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጥበታል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በመጨረሻም የሚጨምሩትና ቀረ የሚሉት ነገር ከአለ?

***መልአከ ገነት በለጠ፦*** አምሰግናለሁ በእውነት ማህበረ ቅዱሳን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል፤ ገዳማትንና የአብነት ት/ቤቶችን በመርዳት፤ ካህናትንና መምህራንን በማፍራት፤ እውቀቱን፣ ጉልበቱንና ገንዘቡን በመስጠት የሚሠራው መልካም ሥራ ብዙ ነውና እግዚአብሔር ከክፉ ነገር ይጠብቅልን እላለሁ፡፡ አሁን በአደረግነው ውይይት ቀረ የምለው ነገር የለም ነገር ግን የሚናገር ሰው ይስታል ዳህፀ ልሳንም ይኖረዋል በጎደለው እግዚአብሔር ይሙላበት ይህንን የሚያነቡ ወገኖች ሁሉ የጎደለውን እየሞሉና እያቃኑ እንዲያነቡት በትህትና እጠይቃለሁ፡፡ በተረፈ እንግዳችሁ በማድረግ ሐሳቤን እንድሰጥ ስለጋበዛችሁኝ በልዑል እግዚአብሔር ስም አመሰግናለሁ፡፡

# "ከትናንቱ በመማር ዛሬ ላይ ጠንክረን ልንሠራ ይገባል"

**- መልአከ ገነት ቀሲስ ንጋቱ**
**የምሥራቅ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ**
**ክፍል ሁለት**

**በእህተ ሚካኤል**

*የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ቃለ መጠይቅ የመጀመሪያ ክፍል ባለፈው እትማችን ላይ ማቅረባችን ይታወሳል፡፡ በዚህ እትማችን ደግሞ ክፍል ሁለትን ይዘንላችሁ ቀርበናል፤ ትከታተሉ ዘንድ ግብዣችን ነው፡፡ የተወደደዳችሁ አንባብያን በመጀመሪያው ክፍል ‹‹ቀሲስ መልአኩ›› ተብሎ የተጻፈው የእንግዳችን ስም ‹‹ቀሲስ ንጋቱ›› መሆኑን እየገለጽን ለተፈጠረው ስህተት ይቅርታ እንጠይቃለን፡፡*

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ሞተ የተባለው እና የተመዘገበው የጥቃቱ ሰለባ የሆነ ሰው ነው?

***መልአከ ገነት ቀሲስ ንጋቱ፦*** አዎን ለምሳሌ አለማያ ላይ አንዲት እናት ሙተዋል፡፡ ቤተ ሰቦቻቸውም ጭንቅላታቸውን ተፈነካክተው እጃቸው ሁሉ ተሰባብሯል፡፡ እናትየው ባልቴት ናቸው፤ በጣም ተደብድበው ስለነበር ሆስፒታል ሲደርሱ ሞቱ፡፡ እንግዲህ በእርሳቸው ስም ፴ ሺህ ብር ቡክ ተከፍቶአል፤ ቡኩ በልጃቸው ወይም በቤተሰቡ ስም መሆን ነበረበት፤ የእርሳቸው ካሳ ለልጆች መሰጠት ነበረበት፡፡ ያው እንደሚታወቀው በሞተ ሰው ስም ሲደረግ ደግሞ ውርስ እና ተያያዥ ነገሮች ሲባሉ ብዙ ጊዜ ይፈጃል፡፡ በእርግጥ ይህ ስለተስተካከለ ችግር የለውም፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ከዚሁ ጋር ተያይዞ የነገዋን ቤተ ክርስቲያን እጣ ፈንታ እንዴት ይገልጹታል?

***መልአከ ገነት ቀሲስ ንጋቱ፦*** የነገዋን ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ባለው እንቅስቃሴ መገመት ይቻላል፡፡ በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን ላይ እየተፈጸመባት ላለው ጥቃት የመንግሥትም እጅ አለበት ነው የምንለው፡፡ እንዲህ ለማለት ያስደፈረን ነገሩን ፊት ለፊት ስላየን እና ስለተረዳን ነው፡፡ ለምሳሌ ጥምቀት በምናከብርበት ጊዜ በታቦታቱ፣ በካህናቱ ላይ ሳይቀር አስለቃሽ ጪስ ይለቀቅ የነበረ፡፡ በዓሉን በሥርዓት የሚያከብረው አካል ላይ ነው ወይስ ነውጥ እየፈጠረ ያለው አካል ነው በአስለቃሽ ጪስ መባረር የነበረበት፤ ነገሩ ግን የተገላቢጦሽ ነበር፡፡ ከትናንቱ ተምረን ዛሬ ላይ ጠንክረን ካልሠራን ነገ የባሰ የማይሆንበት ምንም ምክንያት የለም፡፡



**መልአከ ገነት ቀሲስ ንጋቱ**
**የምሥራቅ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ**

ለምሳሌ ዛሬ ዛሬ በመንግሥት በኩል በተለይ በኦሮሚያ ክልል እኛ ባለንበት በምሥራቁ ከፍተኛ ተጽዕኖ ነው ያለው፡፡ የቤተ ክርስቲያኒቷ ንብረት በሌላ አካባቢ ጠቅላላ ሲመለስ በምሥራቅ ሐረርጌ ግን አልተመለሱላትም ንብረቶቹ የቤተ ክርቲያኒቱ ለመሆናቸው መረጃ ስላለው ነው የምናገረው፡፡ ለቤተ ክርስቲኒቱ የነገ መልካም እጣ ፈንታ ዛሬ ትልቅ ሥራ ከቅዱስ ሲኖዶስ ይጠበቃል እላለሁ፡፡

የቤተክርስቲያኒቱ የበላይ ጠባቂ የሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ ጠንክሮ የቤተ ክርስቲያንን፣ የምእመናንዋን መብት ማስከበር ይጠበቅበታል። ይህ ነገር ካልተደረገ፤ ለቤተ ክርስቲያን እና ለመእመናኗ ጥበቃና ከለላ ካልተደረገ ወደፊት አአስቸጋሪ ነገር ይገጥመናል ብዬ አስባለሁ።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** የቤተ ክርስቲያን ንብረቶች የተወሰዱባት ከዚሁ ከጥቃቱ ጋር ተያይዞ ነው?

***መመልአከ ገነት ቀሲስ ንጋቱ፦*** አይደለም የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ወድቆ ሀገሪቱን የደርግ መንግሥት ሲረከብ በአዋጁ መሠረተ ተብሎ በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ ብዛት ያላቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ ንብረቶች ተወስደውባታል፤ ከዚያ ውስጥ አንዱ በሀረር ከተማ የሚገኙት ንብረቶቿ ናቸው። ለምሳሌ ሁለተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ያሠሩት በሀገረ ስብከቱ መንበረ ጵጵስና ሥር ያለ እና የተማሪዎች አዳሪ ቤት እንዲሁም መማሪያ የነበረ ዘመናዊ ሕንፃ አንዱ ነው። ይህ ሕንፃ እነ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ፣ እነ ቅዱስ አቡነ ጢሞቴዎስ፣ እነ ብፁዕ አቡነ ገሪማ የመሳሰሉ ታላላቅ አባቶች የተማሩበት ትምህርት ቤት ነው የተወረሰው። አሁንም አልተመለሰም የግብርና ጽ/ቤት አድርገው እየሠሩበት ነው።

ሌላ ትምህርት ቤትም ነበረ ትምህርት ቤቶች የሕዝብ መገልገያ ናቸው ስለተባለ ትምህርት ቤቶቹን አልጠየቅንም የቤተ ክርስቲያን ማስረጃ ያላቸውን የተለያዩ ሕንፃዎችን ግን ጠይቀን እስካሁን አልተመለሰልንም። በካቢኔ ተወስኖ መልስ ይሰጥበታል ስለተባለ በተስፋ እየተጠባበቅን ነው።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በቦታው ላይ ያሉ ክርስቲያኖችን የማጽናቱ እና የማበረታታቱ ነገር በሀገረ ስብከቱ ደረጃ እንዴት እየተካሄደ ነው? ወጥ በሆነ ደረጃ እየተሠራ ነው ለማለት ይቻላል?

***መልአከ ገነት ቀሲስ ንጋቱ፦*** እንግዲህ ወጥ የሆነ ሳይሆን ጉዳት የደረሰባቸው አካባቢዎች ላይ ቅዳሜ እና እሑድ እየጠበቅን መምህራንን ሰባክያነ ወንጌልን ከከተማውም ከሀገረ ስብከቱም እያቀናጀን እንዲማሩ፣ እንዲጽናኑ እያደረግን ነው። ሀገረ ስብከቱ ሙሉ አበል የትራንስፖርት እና ልዩ ልዩ ወጪዎችን እየሸፈነ እያገዘ ነው። ጥቃት የደረሰባቸው ቦታዎች ላይ ከአንድም ሁለት ሦስት ጊዜ በአካል በመገኘት አበረታትተናል። ሀገረ ስብከቱ በትምህርተ ወንጌሉም በማጽናናቱም እየሠራ ነው።

ከዚህ በፊት ራስህን ጠብቅ፣ አንተ ተጠንቀቅ እየተባባልን ነበር የምንኖረው። በተለይ የሃይማኖት አባቶችን የበላይ ጠባቂዎችን ይገድላሉ፣ ይመታሉ የሚባል መረጃ ስላለ እና ስለሚወራ ራሳችንን አቀርቅረን፣ዘ ግተን ነበር ያለነው፤ እንደዚህ ዓይነት ችግሮች አሉ። አሁን ባለው እንቅስቃሴ የሕግ የበላይነት ይከበር በሚለው ሂደት ትንሽ ፋታ እያገኘን ነው ያለነው። በአንፃራዊነት ትንሽ ሻል ያለ ሰላም አለ ብዬ አምናለሁ። በተረፈ እግዚአብሔር እርሱ በቸርነቱ ሰላሙን ያምጣ መጨረሻውን ያሳምርልን እላለሁ።

**...ለምሳሌ ጥምቀት በምናከብርበት ጊዜ በታቦታቱ፣ በካህናቱ ላይ ሳይቀር አስለቃሽ ጪስ ይለቀቅ የነበረ። በዓሉን በሥርዓት የሚያከብረው አካል ላይ ነው ወይስ ነውጥ እየፈጠረ ያለው አካል ነው በአስለቃሽ ጪስ መባረር የነበረበት፤ ነገሩ ግን የተገላቢጦሽ ነበር።...**

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በቀጣይስ ምን ለመሥራት ታስቦአል?

***መልአከ ገነት ቀሲስ ንጋቱ ፦*** በቀጣይ በሀገረ ስብከቱ ደረጃ የተወሰነ ነገር አድርጎ ቤት ለመሥራት ቆርቆሮ፣ ሚስማር እና የመሳሰሉትን ለመግዛት እያስተባበርን ነው። አንዳንድ በጎ አድራጊዎች ሲመጡም የሚያሥፈልገንን እየነገርን ቃል እያስገባን ነው። በዚህ አጋጣሚ ማኅበረ ቅዱሳንን ላመሰግን እወዳለሁ፤ ከፍተኛውን ጥረት እያደረጉ ነው፤ ዳታውንም በመሰብሰብ ብዙ ረድተውናል። ለተቃጠሉ አብያተ ክርስቲያናት የቀዳሳያንን አልባሳት ልከዋል። እንዲሁም በቅርብ ጊዜ ውስጥ የገንዘብ እርዳታ አድርገዋል። የተቃጠሉ አብያተ ክርስቲያናትን መልሶ ለመሥራት ዲዛይን አውጥተው ፕላኑን ሠርተው የላኩልን እነርሱ ናቸው። በገንዘብ ሲገመት ከ፫፻፶ ሺህ ብር በላይ ያወጣል፤ እንግዲህ ይኽን ነው ማኅበሩ የሸፈነው። ወደፊት ደግሞ የበለጠ ከኛ ጎን እየሆኑ እንዲሠሩ እንፈልጋለን። አሁንም በእኛ ሥር ሆነው እየሠሩ ነው፤ ቢሮም የሰጠናቸው እኛ ነን፤ በብፁዕነታቸው በአቡነ መቃርዮስ መልካም ፈቃድ አሁንም አስፋፍተው እንዲሠሩ ቦታ ሰጥተናቸዋል። እንግዲህ እጅ ለእጅ ተያይዘን የበለጠ ብዙ ሥራ እንሠራለን ብዬ አምናለሁ።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ፴፱ኛው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ለመካፈል ነው ሀገረ ስብከትዎን ወክለው የመጡት ከጉባኤው ምን አገኙ?

**የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ወድቆ ሀገሪቱን የደርግ መንግሥት ሲረከብ በአዋጁ መሠረት ተብሎ በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ ብዛት ያላቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ ንብረቶች ተወስደውባታል፤ ከዚያ ውስጥ አንዱ በሀረር ከተማ የሚገኙት ንብረቶቿ ናቸው። . . . እነ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፣ እነ ቅዱስ አቡነ ጢሞቴዎስ ፣ እነ ብፁዕ አቡነ ገሪማ የመሳሰሉ ታላላቅ አባቶች የተማሩበት ትምህርት ቤት ነው የተወረሰው። አሁንም አልተመለሰም የግብርና ጽ/ቤት አድርገው እየሠሩበት ነው።**

***መልአከ ገነት ቀሲስ ንጋቱ፦*** ፴፱ኛው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ስብሰባ ከአምናው ትንሽ ለየት የሚለው ሪፖርቶች በየሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጆች ይነበቡ ነበር። ዘንድሮ ግን ያ ቀርቶ ስለ ወቅታዊው የቤተ ክርስቲያኒቷ ሁኔታ ላይ ውይይት እንደምናደርግ ተነግሮን ነበር። እኛም ውይይት እናደርጋለን፣ ሓሳብ እንሰዋወጣለን ብለን አስበን ነበር ነገር ግን ውይይቱ አልቀረበም። በኋላም በኮቪድ ምክንያት ስብሰባውም አጠረ ስለዚህ ምንም የተወያየነውም ነገር የለም። በነበረው ጊዜ የዋና ሥራ አስኪያጁን ሪፖርት፣ የአህጉረ ስብከቱን ሪፖርት ደግሞ በሰበካ ጉባኤው መምሪያ ሓላፊ ነው የቀረበው፤ መሰላቸትም ነበረ። ከዚያም በተጨማሪ ሪፖርቶቹ ተቀንጭበው ስለሚወጡ ሁሉም የራሱ ቅሬታ ውስጥ ነበር። ዋና ዋና መነገር የነበረባቸው ነገሮች አልተነገሩም የሚል ቅሬታዎች ካንዳንድ የጉባኤው አባላት ይነሡ ነበር።

በጉባኤው ላይ ወቅታዊውን የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ያወራነውም ሆነ የተወያየነው ነገር የለም። ቅዱስነታቸውም ቃለ ምዕዳን እና ቡራኬአቸውን ሰጥተው ራሳችንን እንድንጠብቅ እንድንደራጅ የሚል መመሪያ ነው ያስተላለፉት። ከላይ ካነሣሁት ውጪ ፴፱ኛው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በሰላምና በጥሩ ሁኔታ ተጠናቋል ማለት ይቻላል።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** የቅዱስ ፓትርያርኩ መሪ ቃል ራስን ለመከላከል መደራጀት የሚል ነበር መሬት ላይ ወርዶ ተግባራዊ ይሆናል ብለው ያስባሉ?

***መልአከ ገነት ቀሲስ ንጋቱ፦*** መግለጫው ከወጣ በኋላ ቅዱስ ሲኖዶስ በሚኖረው ምልዐተ ጉባኤ ላይ ተወያይቶ በሚያወርደው መመሪያ መሠረት ተግባራዊ ይሆናል ብዬ አስባለሁ። ቅዱስ ሲኖዶስ አጽድቆት በየሀገረ ስብከቱ መመሪያ ሲተላለፍ በዚያ መሠረት ተግባራዊ ለማድረግ ሁሉም የቻለውን ሁሉ ይሠራል።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** እንደ አጠቃላይ ቀረ የሚሉት እና የሚጨምሩት ነገር ካለ?

***መልአከ ገነት ቀሲስ ንጋቱ፦*** ቀረ ሳይሆን ትኩረት እንዲሰጠው የምፈልገው ከላይ ያነሳሁት በሀገረ ስብከታችን ለጥቃት የተጋለጡትና እርዳታው ሳይደርሳቸው የቀሩት ምእመናን በሙሉ ተካተው እርዳታውን የሚያገኙበት መንገድ ቢፋጠን እላለሁ።


ሌላው በሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤው ላይ ስለተካሄደው ሽልማት ማንሳት ፈልጋለሁ። በሽልማቱ ዙሪያ ተጨባጭነት ያለው ሥራ ቢሠራ ጥሩ ነው እላለሁ። አንድ አህጉረ ስብከት ከመሰሉ አህጉረ ስብከት ጋር ነው መወዳደር ያለበት ብዬ አምናለሁ። ለምሳሌ ምሥራቅ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ያሉት አብያተ ክርስቲያኖች ፶፫ ወረዳዎቹም አምስት ናቸው በጣም አናሳ አብያተ ክርስቲያናት ያሉት የምሥራቅ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ከሀዋሳ እና ከድሬ ዳዋ ሀገረ ስብከት ጋር ውድድር ውስጥ መግባት የለበትም። ከሚመሳሰለው ጋር ነው መወዳደር የነበረበት እላለሁ። አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በኦሮሚያ ክልል መከራና ፍዳ የደረሰባቸው ብዙ ነገር ተጋፍጠው በእሳት ውስጥ ያለፉ ሀገረ ስብከቶች ባላቸው አቅም ሠርተው ሪፖርት ማቅረባቸው በመሸለም ሞራል ሊሰጣቸው ይገባ ነበር። ይኽ ቅሬታን ያመጣል፤ እገሌ እገሌ ከማለት ይልቅ ለሁሉም የተሳትፎ የምሥክር ወረቀት ሰጥቶ መሸኘት ይሻል ነበር።

የመጨረሻው ቤተ ክርስቲያን አሁን ያለችበት ነባራዊ ሁኔታ በቅዱስ ሲኖዶስም ሆነ ማንኛውም የቤተ ክርስቲያኒቱ አካላት ችላ መባል የለበትም። ካለፈው በመማር ራስን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው እላለሁ። እኔ ስለፖለቲካ ብዙ አላውቅም ። የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ባለው የመንግሥት የሥልጣን እርከን ላይ ብዙም አይታዩም ጭራሽ የሉም ማለት ይቻላል። ይኽ ይመስለኛል በተወሰነ መልኩ ቢሆን ሃይ ባይ በሌለበት ቤተ ክርስቲያኒቱን ለጥቃት ያጋለጣት እና ያስጠቃት። ቢያንስ አንድ ሁለት ሰው ቢኖር መከላከል አልፎም አስቀድሞ መረጃ ማግኘት እና ራስን መጠበቅ ይቻል ነበር ብዬ አስባለሁ።

የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ከፊታችን የሚመጣውን ሀገራዊ ምርጫ በቸልታ ሊያልፉት አይገባም። አጋጣሚውን እንደ በጎ እድል በመውሰድ በምርጫው ላይ የቤተ ክርስቲያንቱን ልጆች በመምረጥም ሆነ በመመረጥ ተሳትፎ ማድረግ ይገባል። በየትኛውም ጉዳይ ላይ ቸል ልንል አይገባም፤ ቸልተኝነት ዋጋ እንዳስከፈለን አይተናልና። ጠንክረን ሁላችንም በያለንበት ለምርጫው ትኩረት ሰጥተን ብንሠራበት ጥሩ ነው የሚል ግንዛቤ አለኝ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ።

# የብዙዎች አባት - አቡነ ኢየሱስ ሞዐ

በቀሲስ ዘክርስቶስ ፀጋዬ



የተወዳዳችሁ የእግዚአብሔር ልጆች! እንደምን ሰነበታችሁ? አሜን፤ የአባቶቻችን የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን!

ልጆች! ዛሬ የብዙ ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን መንፈሳዊ አባት ስለሆኑት ጻድቁ አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዐ ታሪክ ይዘንላችሁ ቀርበናል፤ የቅዱሳንን ታሪክ በማንበብ ለቅዱሳን ከተሰጠው ቃል ኪዳን ተጠቃሚ መሆን ይቻላልና በጥሞና ታነቡ ዘንድ እንጋብዛችኋለን!

የአቡነ ኢየሱስ ሞዐ አባታቸው ዘክርስቶስ እናታቸው ደግሞ እግዚእ ክብራ ይባላሉ:: በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ:: አቡነ ኢየሱስ ሞዓ በጐንደር ክፍለ ሀገር ዳኅና ገብርኤል በሚባል ቦታ ግንቦት ፳፯ በ፲፪፻፲ ዓ.ም ተወለዱ::

ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ በአባታቸው ቤት እና በአካባቢያቸው ጥበብን፣ ትምህርተ ሃይማኖትን እና መልካም ተግባርን ሁሉ እየፈጸሙ አደጉ:: በቅድስና በንጽሕና ሆነው በቤተሰቦቻቸው ቤት እስከ ሠላሳ ዓመት ኖሩ::

አንድ ቀን ስሙ ገብርኤል የተባለ የእግዚአብሔር መልአክ ለአቡነ ኢየሱስ ሞዐ በሌሊት ታያቸው:: ሦስት ጊዜም ጠራቸውና ‹‹ከአባትህ ቤት ውጣ፤ ወደ ታላቁ አባት ወደ አባ ዮሐኒ መኖሪያ ወደ ደብረ ዳሞ ገዳም ሂድ፤ ደግ አገልጋይ ትሆናለህም›› አላቸው:: ቃሉንም ተቀበሉትና በሠላሳ ዓመታቸው በ፲፪፻፵ ዓ.ም. ወደ ደብረ ዳሞ ገዳም ገብተው ከአባ ዮሐኒ ጋር ሰባት ዓመት ኖሩ::

ልጆች! አቡነ ኢየሱስ ሞዐ አባ ዮሐኒን ሌሎች መነኰሳትን እየረዱና መደበኛ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ለሰባት ዓመት ቈይተው ከደብረ ዳሞ ገዳም አበምኔት ከአባ ዮሐኒ በሠላሳ ሰባት ዓመታቸዉ በ፲፪፻፵፯ ዓ.ም. መዓረገ ምንኲስናን ተቀበሉ::

አቡነ ኢየሱስ ሞዐ በጽድቅ እና የሊቅነት ሕይወት የሚኖሩ ታላቅ አባት ናቸው:: በዘመናቸው ለቤተክርስቲያንም ብዙ ሥራዎችን ሠርተዋል፤ ይህ ሥራቸውም በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቷል::

ከዕለታት በአንድ ቀን ደግሞ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ተገልጾ ገድላቸውና ትሩፈታቸው በዓለም ሕዝብ ሁሉ እንደሚታወቅ ነግሯቸው ‹‹የስምህ መከበሪያ ወደ ሆነዉ ሐይቅ ወደ ተባለዉ ሥፍራ ተነሣና ሂድ›› አላቸው፡፡

የብዙ ወራት መንገድ የሆነውንም እርሱ እየመራ በስድስት ሰዓት ዉስጥ ከሐይቅ ከተማ አደረሳቸውና ተሠወረ፡፡ ከዚያም በኋላ ከሐይቅ ገዳም በስተሰሜን አቅጣጫ ወደ በሚገኘው ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ገብተው ለስድስት ወራት ያህል ቀን ቀን ሕዝቡን ሲያስተምሩ በመዋል ሲመሽ ወደ ሐይቅ በመግባት ሲጸልዩ ያድሩ ነበር፡፡

ከዚህ የተነሣ በሐይቅ እስጢፋኖስ አካባቢ ይኖሩ የነበሩት መነኰሳት ማታ ማታ የብርሃን ዓምድ ወደ ሐይቁ ሲገባ ማለዳ ደግሞ ሲወጣ ያዩ ነበር፡፡ በዚህ ዓይነት ክብራቸዉ የተገለጠዉ አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዐ በልዑል እግዚአብሔር ፈቃድና በገዳሙ አባቶች ተማኅጽኖ የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም አበምኔት ሆነው ተሾሙ፡፡

አቡነ ኢየሱስ ሞዐ ከተሾሙበት ዕለት ጀምሮ ለገዳሙ እንዲሁም ለመላው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የተለያዩ መልካም ተግባራትን እየሠሩ ለ፵፫ ዓመታት አገልገለዋል፡፡

አባታችን ከሠሯቸው ሥራዎች መካከልም ልዩ ልዩ ቅዱሳት መጻሕፍትን በመጻፍና በማሰባሰብ በሐይቅ ገዳም በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን መንፈሳዊ የቤተክርስቲያን ቤተ መጻሕፍት አቋቁመዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የመጀመሪያውን ቋሚ የአብነት ትምህርት ቤት በማቋቋም ስምንት መቶ መነኮሳትን በትምህርተ ሃይማኖት በማነጽ በመላው ኢትዮጵያ አሰማርተዋቸዋል፡፡ ከእነዚህም መነኰሳት መካከል፣ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ አቡነ ኂሩተ አምላክ፣ አባ በጸሎተ ሚካኤል የመሠሰሉትን እጅግ በጣም ብዙ ደጋግ አባቶችን አፍርተዋል፤ በዚህም የተነሣ ‹‹ወላዴ አእላፍ›› የብዙዎች አባት ተብለው ይጠራሉ፡፡

በመጨረሻም ከእግዚአብሔር ‹‹በስምህ ግማሽ እንጀራና ቀዝቃዛ ውኃ ለድሆች የሰጠውን እስከ ሰባት ትውልድ እምርልሃለው›› የሚልን ቃል ኪዳንን ከፈጣሪያቸው ተቀብለው በ፹፪ ዓመታቸው ኅዳር ፳፮ ቀን ፲፪፻፺፪ ዓም በዕለተ እሑድ ዐርፈዋል፡፡ ‹‹በዚያችም ዕለት በቦታው የታየው የብርሃን ዓምድ ሀገሪቱን ሞላት›› በማለት በስማቸው የተጻፈው ገድለ ኢየሱስ ሞዐ ይተርካል፡፡

ልጆች! ከብዙዎች አባት ከአባታችን ከአቡነ ኢየሱስ ሞዐ ታሪክ ብዙ ትምህርት እንደተማራችሁ ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ወር በገባ በ፳፮ ከአቡነ ሀብተ ማርያም ጋር በዓላቸው ይታሰባልና እናንተም አቡነ ኢየሱስ ሞዐን በመዘከር ረድኤት በረከት እንድታገኙ እናሳስባችኋለን፡፡

*በሚቀጥለው ትምህርታችን እስክንገናኝ*

*ደኅና ሰንብቱ!*

*የአቡነ ኢየሱስ ሞዐ አምላክ ከእናንተ ጋር ይሁን!*

# ያልተቆጠረው ሀብት

ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ

አንድ ምሽት በምሥራቅ የኦሮሚያ አካባቢ ባሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አህጉረ ስብከቶች ስላሉ ክርስቲያኖች መከራና የስጋት ሕይወት እያሰብኩ ሳለ አንድ ሐሳብ መጣልኝ፤ በእነዚህ ሀገረ ስብከቶች ለአደጋ የተጋለጡ ስንት አብያተ ክርስቲያናት ይኖሩ ይሆን? ማን ማን ይባሉ ይሆን? ምን ያህልስ ምእመናንና ካህናት ይኖሩ ይሆን? አልኩ፡፡

ወዲያውኑ ስልኬን ከፍቼ የኢንተርኔቱን የመረጃ መስጫ መረብ ተቀላቀልኩ፡፡ በተለመደው መንገድ በጎግል ልፈልግ ብዬ የሀገረ ስብከት ስምና የቤተ ክርስቲያን ቃላት ዓይነት እያማረጥኩ አሰሳዬን ቀጠልኩ፡፡ ነገር ግን አልፎ አልፎ መከራ ስለደረሰባቸው አንዳንድ አጥቢያዎች በግርድፉ ከሚጠቅሱ የዜና ዘገባዎች ውጪ መሠረታዊ መረጃ የያዘ ገጽ ድርም ሆነ የጥናት ጽሑፍ ማግኘት አልቻልኩም፡፡ ሀገረ ስብከቶቹ ራሳቸውን የሚገልጹበት፣ አጥቢያዎች ስለአሉበት ሁኔታ የሚነግሩበት አንድም የማኅበራዊ ሚዲያ ሽፋን የለም፡፡ ለምን? ከዚያ አልፌ በጠቅላይ ቤተ ክህንት ደረጃ እነዚህን መሠረታዊ መረጃዎች በቀላሉ ተደራሽ የሚያደርግ ገጸ ድር ወይም ጥናት ላገኝ አልቻልኩም፡፡

ወዳጆቼ! የተቀነሰብንን፣ ያጣነውን፣ የተቸገርንበትን ነገር መጠኑን የምናውቀው የነበረንን በውል ስናውቅ ነው፡፡

ስንት አህጉረ ስብከቶች ነበሩን? አሁን ስንት አሉን? በእነርሱ ሥር ስንት ወረዳ ቤተ ክህነቶች አሉ? በእነርሱ ሥር ስንት አጥቢያዎች አሉ? ከእነርሱስ ስንት ገዳማት ስንት ደብሮች ስንት የገጠር አብያተ ክርስቲያናት አሉን? መቼ ተሠሩ? መቼ ታደሱ? በእነርሱስ ስር ምን ያህል ቀሳውስት፣ ዲያቆናት፣ መርጌቶች ...አሉ? እነርሱስ የሚያገለግሏቸው ምእመናን ቁጥር ስንት ነው? ስንቶቹስ ከአጥቢያቸው ጋር ጥብቅ ቁርኝት አላቸው? ለእነዚህ ጥያቄዎች የምንሰጠው መልስ ያለንን ሀብት መጠን እንድናውቅ ይጠቅመናል፤ ይህ ግን በጥቂቱም ይሁን ተሟልቶ የተሠራው በየትኛው ሀገረ ስብከት ነው? ከተሠራውስ ምን ያህሉን ግልጽ አድርገናል?

ይህ ከሌለን ዛሬ ወይም ነገ የሚጎድልብንን ማወቅ አንችልም፡፡ ይህንን ማወቅ ብንችል ባለፉት ፴ ዓመታት እንኳን ከነበረን ምን ያህል እንዳጣን ለመተንተን ይመች ነበር፡፡ ዛሬ መከራ እና ስጋት አለባቸው በምንላቸው አህጉረ ስብከቶች ካሉ አጥቢያዎች ምን ያህሉ ተቃጠሉ ተዘጉ ብለን በስም ጠቅሰን ለማዘን ለማሳሰብ ለመጸለይም ይበጀን ነበር፡፡ ከእነዚህ ከተጎዱ አህጉረ ስብከት የተሰደዱ ካህናት እና ምእመናን ስንት ናቸው? ቤተክህነትን በመሰለ ተቋም ውስጥ ‹‹ቤት ይቁጠረው›› ብሎ ማለፍ ያሳፍራል፡፡ እያንዳንዱ የእኛ ቤት ነውና ቤተ ክህነት እንደ አንድ ቤተሰብ ሊቆጥረው ሊያውቀው እና ሊያሳውቀው የሚገባ ነበር፡፡

ዛሬ ብቻ ሳይሆን ትናንትም ስንታዘበው የነበረው ጉልህ እውነታ አለ፡፡ የቤተ ክርስቲያን ቅርሶች በአፅራረ ቤተ ክርስቲያንና በሌቦች ብዙ እንደተመዘበሩ ስንተርክ ነበር፤ አሁንም እንተርካለን፡፡ ነገር ግን በእርግጠኝነት የተጎዳንበትን ልክ እናውቀው ይሆን? እንዴት አድርገን? ቀድመን በየአጥቢያዎቻችን ያሉ ቅርሶችን መዝግበን ቆጥረን ሰፍረን መቼ አወቅን! ያን ብናውቅ ስንቱ በቃጠሎ፣ ስንቱ በስርቆት፣ ስንቱ በአያያዝ እንደጠፋ አውቀን እናለቅስ ነበር፡፡ ይህ ሁሉ ግን ባለመሆኑ ትዝብት ላይ ጥሎናል፡፡

ያለንን ቆጥረን ሰፍረን ማወቅ ያለብን ለማዘን ብቻ አይደለም፤ እግዚአብሔርንም ለማመስገን ነው፡፡ የነበሩንን የምእመናን ቁጥር አውቀን ቢሆን ሰብከን ያመጣናቸውን፣ አስተምረን ያጠመቅናቸውን አዳዲስ አማንያን ቁጥር እየተናገርን እግዚአብሔርን እናመሰግን ነበር፤ እንደ ሐዋርያትም ‹‹ በጌታችንም የሚያምኑ ብዙዎች ይጨመሩ ነበር፤ ወንዶችና ሴቶችም ብዙዎች ነበሩ፡፡(የሐዋ ፭፥፲፬ ) እያልን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ እንመሰክር ነበር፡፡

ወደፊት አቅዶ ለመሥራትም ያለንን ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ በየጊዜው ቤተ ክህነት በሚያቀርበው ሪፖርት ለምሳሌ በዚህ ዓመት ጠቅላይ ቤተክህነት ብቻ ፫፻፶ ሚሊየን ብር ያህል ‹‹ፐርሰንት›› መሰብሰቡን የሰማነውን ያህል ከትናንት ዛሬ ስለተጨመሩልን ምእመናን፣ ስለተሠሩ አብያተ ክርስቲያናት ቁጥር በየሀገረ ስብከቱ ለጥምቀት ስለተዘጋጁ ንኡሰ ክርስቲያን በየደረጃው ወጥቶ ዜና የሆነ ቁጥር አለን?! የለንም፡፡ ለምን? ትዝብት ላይ የሚጥል ነው፡፡

ቤተ ክህነት ተከታዩን ምእመን ቁጥር በውል ያውቀዋል? ስንት ካህናት አሉን? ይህንን እንደተጠየቀ ‹‹ይህን ያህል ሺህ አካባቢ፣ ይህን ያህል ይገመታል፤ እጅግ ብዙ…›› ወዘተ እያሉ ከመናገር ተላቆ ወይም ሺህና መቶ እያሉ በድፍን ከመቁጠር ርቆ በትክክል ይህን ያህል ነው ብሎ መናገር የሚችል ይኖር ይሆን?

**ያለንን ቆጥረን ሰፍረን ማወቅ ያለብን ለማዘን ብቻ አይደለም፤ እግዚአብሔርንም ለማመስገን ነው፡፡ የነበሩንን የምእመናን ቁጥር አውቀን ቢሆን ሰብከን ያመጣናቸውን፣ አስተምረን ያጠመቅናቸውን አዳዲስ አማንያን ቁጥር እየተናገርን እግዚአብሔርን እናመሰግን ነበር፤**

በዚህ ዓመትስ ስንት ካህናት ተሾሙ በየት ሀገረ ስብከት? እነማን ናቸው? ይህ ሁሉ መታወቅ ያለበት እውነት ነው፡፡ ሕዝብ ካህኑን ሳያውቅ ካህን መስሎ በመጣው ሁሉ ግራ የሚጋበው እኮ በአደባባይ እያንዳንዱ አጥቢያ ወይም ወረዳ ቤተ ክህነት በሥሩ ያሉትን ካህናት ማንነት በፎቶግራፍ ጭምር አስደግፎ በአደባባይ ስለማይገልጽ ነው፡፡ ምነው ይህንን እንኳን ከአኃት አብያተ ክርስቲያት ብንማር! እነርሱ የተሾመውን ብቻ ሳይሆን ያጨቻቸውን በአደባባይ ምስክርነት እንዲሰጥላቸው ያደርጉ የለምን? ነቀፋ ከተገኘበትስ ሳይሾም ያቆዩት የለም እንዴ!

ይህ ሁሉ ለትዝብት የሚዳርግ ሰንፍና ለምን ሆነብን ስንል ስላልሠራን ብቻ ሳይሆን የሠራነውን ወይም ያልሠራነውን ስለማንቆጥር፣ ቆጥረንም ቢሆን ይፋ ስለማናደርግ፣ አድርገንም ቢሆን ለውጦችን (update) ስለማናካትት ነው፡፡ ለምን አንቆጥርም? ጥቅሙን ባለማወቅ? ጽድቅ ስለሆነ? በስንፍና? ይህን ራሳችንን መመርመር ይገባናል፡፡ ይህንን ካላደረግን ሰዎችስ ስለእኛ እንዴት ይወቁ? ጋዜጠኞችስ ስለእኛ ደስታም ሆነ ሐዘን እንዴት ይዘግቡ? ተመራማሪዎች ስለእኛ እንዴት ያጥኑ ?….

የማንቆጥረው በአስተምህሮ ምክንያት ነው እንዳንል ‹‹ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው የእስራኤልን ልጆች በሰፈር ሁሉ ቈጠረ፡፡›› (ዘኍ ፫፥፴፪) ብለን እናስተምራለን፡፡ አሪት ዘኍልቍ የሚለው መጽሐፍም የቅዱሳት መጻሕፍት አንድ አካል ባልሆነ ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ወገን በሰላሙ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በመከራው ጊዜ እንኳን የእርሱ የሆነውን ቆጥሮ ሰፍሮ ያውቃል፡፡ ልጆቹንና ሀብቱን ሁሉ በቁጥር ብቻ ሳይሆን በስምም ማወቅ አለበት! ‹‹የባቢሎንም ንጉሥ ናቡከደነፆር ወደ ባቢሎን ከማረካቸው ምርኮኞች ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ ይሁዳ ወደ እየከተማቸው የተመለሱት የሀገር ልጆች እነዚህ ናቸው፡፡›› (ዕዝራ ፪፥፩) የተባለውን የምታነብ ቤተ ክርስቲያን ነችና፡፡ ቤተ ክህነት ልጆቹን ስንትና እነማን እንደሆኑ ማወቅ፣ መግለጽ ይገባዋል ክርስቶሳዊ ነውና ‹‹ የእናንተስ የራስ ጠጕራችሁ ሁሉ የተቈጠረ ነው፤›› (ሉቃስ ፲፪፥፯) ያለውን ክርስቶስን መምሰል አለበት፡፡ ‹‹ልጄ ጠፋ፣ የጠፋው ልጄ ተመለሰ›› ለማለትም የሚመቸው ልጆችን በውል ሲያውቅና ሲያሳውቅ ነው፡፡

ስለዚህ ዘርን ሳይሆን የቤተ ክርስቲያንን ሀብት መቁጠር እንልመድ፡፡ የምንቆጥረው ለመመካት አይደለም ለመጠበብ እንጂ፡፡ ሰላሙን ይስጠን፡፡

# ብቸኝነት እየጎዳኝ ነው

**ክፍል አንድ**

ይድረስ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ አዘጋጆች፤ እንደምን ሰነበታችሁ? እኔ እግአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ፤ ስሜ ወለተ መድኅን ይባላል ዛሬ ለዓመታት ሲያስጨንቀኝ እና ሲያሰቃየኝ የነበረ ችግሬን ሳካፍላችሁ መፍትሔ የያዘ ምላሽ ትሰጡኛላችሁ ብዬ በማመን ነው::

በወጣትነት ዕድሜ ላይ ነው የምገኘው፤ ከልጅነቴ ጀምሮ ተግባቢና ተጫዋች የምትባል ዓይነት ሴት ነበርኩ:: በትምህርት ቤት በነበርኩበት ጊዜ ብዙ ጓደኞች ነበሩኝ፤ ብቸኛ የሆንኩበትንም ወቅት አላስታውስም:: በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ይህ ችግር አላጋጠመኝም:: ወደ ሥራ ዓለም ገብቼ ከተለያዩ ማኅበረሰብ ውስጥ መኖር ስጀምር በተለያዩ አጋጣሚ የቀርብኳቸው ሰዎች ኑሮአቸው ከጥቅም ጋር የተያያዘ መሆኑን ተረዳሁ፤ ያ ብቻም አይደለም፤ ሰዎች ሠርተው እና ለፍተው ከማግኘት ይልቅ በአቋራጭ ለመክበር እንደሚጥሩ ሳይ በመጀመሪያ ላይ ተቸግሬ ነበር፤ ሥራዬ ላይም እክል ሆኖብኝ ነበር፤ ገንዘብን ለማግኘት እና ሀብትን ለማካበት ሲሉም በሥልጣናቸው ጭምር ተጠቅመው ሠርቶ ማደር የሚፈልገውንና የሚጥረውን ሰው የሚበድሉ፤ ለሌሎች ከማዘን ይልቅ የሰዎችን ኑሮ ከሚበጠብጡ ሰዎች ጋር ተግባብቶና ተስማምቶ ለመሥራት እጅጉን ተቸግሬ ነበር::

ከትምህርት ጓደኞቼ ጋር በሥራ ቦታችን መለያየት የተነሣ በመራራቂ ከሥራ ቦታም ሆነ በተለያዩ ሥፍራዎች ጓደኛ ማግኘት አልቻልኩም:: ጥሩ ሰዎች ናቸው ብዬ የቀረብኳቸው እና ለጓደኝነት ይሆኑኛል ብዬ ያሰብኳቸው ሴቶች እውነተኛ ሆነው ስላላገኘኋቸው ምንም ዓይነት ማኅበራዊ ሕይወትን ከእነርሱ ጋር ማሳለፍ ተሳነኝ:: ጓደኛ ማጣቴም እጅጉን ጎድቶኛል:: በሥራ ወይም በግል ሕይወቴ ላይ የተለያዩ ዓይነት ስሜትን የሚጎዳ ንግግር እንዲሁም አስተያየት በመስጠት እና በመዝለፍ እኔን ለመጉዳት የሚጥሩ ሰዎችም እንዲሁ ሕይወቴን አስቸጋሪ አድርገውብኝ ነበር:: በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሥራ እና የግል ሕይወቴን የሚያስተጓጉሉ ድርጊትም ከመፈጸም ወደ ኋላ አይሉም፤ ይህ ሁኔታ አልፎም ለትዳር ያለኝን አመለካከት እስከ ማበላሸትም የደረሰበት ጊዜ ነበር:: በዚህም የተነሣ በፍቅር ሕይወቴ በመጎዳቴ ትዳር ለመመሥረት ፍላጎት እስከማጣት ደርሻለሁ:: በመሆኑም ከዚህ ሁሉ ችግር በኋላ ሰዎችን ርቄ ብቻዬን ለመኖር ወሰንኩ:: ቤተሰቦቼም ከእኔ ጋር ስለማይኖሩ በብቸኝነት ኑሮዬን እየገፋሁ ነው:: የዕረፍት ቀኔንም ሆነ ትርፍ ጊዜ በማገኝበት ወቀትም ብቻዬን አሳልፋለሁ:: ነገር ግን ማንም ቢሆን ሰው ያስፈልገዋልና ብቸኝነት እየጎዳኝ ነው:: ስለዚህ ምን ትመክሩኛላችሁ?

ውድ እኅታችን ወለተ መድኅን ምክር አስፈላጊና ጠቃሚ እንደሆነ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት በብዙ ቦታ ተጽፎ እናገኛለን:: "ብልህ ሰው ያለ ምክር የሚሠራው ሥራ የለም፤ የሚሠራውም ሥራ የበጀ ይሆንለታል:: " (ሲራክ. ፴፯÷፲፮ )

የሚለው ከእነርሱ መካከል አንዱ ነው:: አንቺም ለገጠመሽ ፈተና መሻትሽ መልካም ነው ::

ውድ እኅታችን ብቸኝነት በተለያየ መንገድ በሰዎች ላይ ሊከሠት ይችላል:: ሰዎች የሚወዱአቸው ሰዎች በሞትም ሆነ በሕይወት ሲለዩአቸው፣ ከጋብቻ ጋር በተያያዘ በቤተሰብ መሀል ፍቺ ሲኖር እና ቤተሰብ ሲለያይ፣ በሰዎች መካከል የአመለካከት እና የአስተሳሰብ ልዩነት ሲኖር እና ያንን አቻችሎ መኖር ሲያቅት አንደኛው ወገን ከሌሎች ጋር ላለመገናኘት በመወሰን ለመሸሽ በሚያደርገው ጥረት ውስጥ ወደ ብቸኝነት ሊገባ ይችላል::

አንዳንዶች ከደረሰባቸው ክፉ ነገር ተነሥተው የቀደመውን ዓይነት ችግር ውስጥ ደግመው ላለመግባት ከሰዎች ጋር መገናኘቱን በመተው ብቸኝነትን ይመርጣሉ:: ሆኖም ሰዎች ከሰዎች እየራቁ በሄዱ ቁጥር ባዶነት እየተሰማቸው ይሄድና በመጨረሻ ለከፋ የሥነ ልቡና ችግር ሊያጋልጣቸው ይችላል::

ከሰዎች ጋር ባለው ግኙኝነት ከሚመጣባቸው የብቸኝነት ተጽእኖ ውጪ በራሳቸው አማካይነት ሊከሠትም ይቻላል:: ለምሳሌ ሰዎች የአእምሮ ሕመም ሲያጋጥማቸው፣

**በእርግጥ ሰዎች ሁሉ አንድ አይደሉም እንደ መልካቸው ሁሉ ባሕሪያቸው ሊለያይ ይችላል:: አንቺም ከአንድ ወይም ከሁለት ሰው ጋር በነበረሽ ግኙኝነት ሁሉም ሰው እንደዚያ ዓይነት ባሕርይ ይኖረዋል ብለሽ መገመት የለብሽም:: ከጥቂት ሰዎች ጋር በነበረሽ ግኑኝነት ሁሉም ሰው እንደዚያ ዓይነት ነው ብለሽ መገመትሽ ሰዎችን ሁሉ እንድትርቂ እና ብቸኛ እንድትሆኚ አድርጎሻል::**

ሥራ አጥነት ሲከሠት፣ የአካል ጉዳተኝነት . . . ወዘተ የመሳሰሉት ለብቸኝነት ሊጋለጡ ይችላሉ::

ወደ እኅታችን ወደ አንቺ ጥያቄ ስንመጣ ችግርሽን በጽሑፍ እንደገለጽሽው ከልጅነት ጀምሮ ተጫዋችና በትምህርት ቤትም ብዙ ጓደኞች እንደነበሩሽ፤ ወደ ሥራ ዓለም ገብተሽ የቀረብሻቸው ሰዎች ግን፦

፩ኛ. ለግል ጥቅማቸው ብቻ የሚያተኩሩ፣ ለፍተው ከማግኘት ይልቅ በአቋራጭ ለመክበር የሚፈልጉ፣ በሥልጣናቸው ጭምር ተጠቅመው ሌሎችን የሚበድሉ መሆናቸው፤

፪ኛ. ለጓደኝነት የምትቀርቢያቸው ሴቶችም፤ እውነተኞች ባለመሆናቸው ጓደኛ በማጣት መቸገርሽን፤

፫ኛ. በሥራና በግል ሕይወትሽ ስሜትሽን የሚጎዱ አስተያየት በመስጠትናበመዝለፍ፤ ሕይወትሽን አስቸጋሪ እንዳደረጉብሽ፤

፬ኛ. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሥራና የግል ሕይወትን የሚያስተጓጉሉ ድርጊቶች ከመፈጸም አልፎ፤ ለትዳር ያለሽን አመለካከት እስከማበላሸት መድረሳቸው፤ በዚህም የተነሣ ትዳር ለመመሥረት መቸገርሽን፤

፳ኛ. በመጨረሻም ከሰዎች ርቀሽ በብቸኝነት ለመኖር መወሰንሽንና የዕረፍት ጊዜሽን በብቸኝነት እያሳለፍሽ መሆኑን፤ ነገር ግን ብቸኝነቱ እየጎዳሽ ስለሆነ፤ ሰው የግድ እንደሚያስፈልግሽ ስለተረዳሽ፤ ምክር እንድናካፍልሽ ጠይቀሻል፡፡ በዚህም መሠረት እኛ ጥያቄሽን ተመልክተን ችግርሽን ተረድተን ለጥያቄዎችሽ መልስ ይሆናሉ ያልናቸውን ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከአባቶች አስተምህሮ ጥቂቶቹን የመፍትሔ ሐሳቦች እንጠቁምሻለን፡፡

፩. በመሥሪያ ቤት ውሎሽ የገለጽሽው ሐሳብ በተለይ በሠራተኞች አካባቢየተመለከትሽው መጥፎ ባሕርያት በተለይ በዘመናችን በብዙዎች ላይ የሚታይ መሆኑ ነው፡፡ ባንቺ በኩል የሚሰሙሽ ከሆነ ለመምከር መሞከር ነው፤ የማይሰሙሽ ከሆነ ግን ከክፉ ሥራቸው መለየት ነው፡፡ "ከክፉ ሽሽ መልካሙን አድርግ፤" ይላልና (መዝ. ፴፫፥፳፯) እኛ የሰው ልጆች የተፈጠርነው፤ አምላካችን የሚወደውን፣ የሚፈቅደውን ፈጽመን የመንግሥቱ ወራሾች እንድንሆን ነበር፡፡ ነገር ግን የጠላት ዲያብሎስን ምክር በመከተል፣ ለፈቃደ ሥጋ በመሸነፍ፤ ራሳችንንም ሌሎችንም በመጥፎ ሥነ ምግባራችን በመፈተንን ላይ እንገኛለን፡፡

እኅታችን ወለተ መድኅን ሰዎች አንቺን በበጎ ማየት አቁመው በምትሠሪው ሥራ ሲመቀኙሽ፣ መጥፎም ሊያደርጉብሽ ቢሞክሩ የተሻለ ነገር በመሥራት ከቀድሞው በበለጠ ሥራሽን በማሻሻል እና በክፉ የሚያዩሽን ሰዎች በቅንነት በመቀበል በአንቺ ላይ ያላቸውን አመለካከት መቀየር ትችያለሽ፡፡ በተሰለፍሽበት የሥራ መስክ ውጤታማ ለመሆን በምታደርጊው እንቅስቃሴ ባንቺ ጉዳይ ጣልቃ ይገቡ የነበሩ ሰዎች ተስፋ ቆርጠው ሊተዉ ይቻላሉ፡፡ በተለይ በራስሽ የምትተማመኚ ሆነሽ ከተገኘሽ ሌሎችን በመልካም ወደራስሽ መሳብ ትችያለሽ፡፡

እኅታችን ወለተ መድኅን ከላይ የተነሡት ምክረ ሐሳቦች እንደተጠበቁ ሆነው የመድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ልጅ እንደመሆንሽ እርሱን አርአያና ምሳሌ በማድረግ የምትጠይው ሰዎቹን ሳይሆን ክፉ ተግባራቸውን መሆን አለበት፡፡ በዘወትር ጸሎትሽም "በክፉዎች ግብር እንዳልሳብ ጠብቀኝ፤ ክፉ ከሚያሠራቸው ከፈቃደ ሥጋ፣ ከሰው ልጆች ባላጋራ ሰይጣን ነፃ አውጣኝ" በማለት ጸልዩ፡፡ ይህን ስታደርጊ በእነሱ አድሮ የሚፈትንሽ ሰይጣን ገለል ይልልሻል፤ ጠላት ሰይጣን በግልጽ ሊፈትነን አይመጣም፤ ሕይወታችን ሰላማዊ እንዳይሆን፤ በደካማ ጎናችን እየገባ በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠርን ሰዎች ስምምነት እንዳይኖረን፣ እንዳንግባባ፣ አንዳችን በሌላው እንድንፈርድ እያደረገ ይዋጋናል፡፡ ይህን እውነተኛ ጠላታችንን ልናውቅበት ይገባል፡፡ ይቀጥላል...